# የእግዚአብሔር ፅድቅ የእኛ መቤገዤት

**በጃኪይ ኦሼ**
**የተዘጋጀ**

## ከእዝራ፤ ከነህምያ እና ከነብያት መፃህፍት እና ምዕራፎች የተወሰዱ ታሪኮች


ትምህርት 1፡ እግዚአብሔር ሲመለከት …… እግዚአብሔር ተወ — ዮናስ

ትምህርት 2፡ ከሁሉ በላይ የሆነው የእርሱ አገልጋዮች…… ዳንኤል እና ጓደኞቹ

ትምህርት 3፡ የህያው አምላክ አገልጋይ…… ዳንኤል እና ንጉስ ዳርዮስ

ትምህርት 4፡ ለዚህን ጊዜ…… አስቴር

ትምህርት 5፡ የእግዚአብሄር መልካም እጅ — እዝራ

ትምህርት 6፡ አንተ ፃዲቅ ነህ— ነህምያ


"…አንተን እንዳልበድል ቃልህን በልቤ ሰወርሁt…"

መዝሙር 119:11

በቴንዝ ፖወር ፐብሊሺንግ የተዘጋጀ

©2015 በክሮስ ኮኔክት አገልግሎት

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

# መቅድም

አስደናቂ የሆነውን የህይወት ጉዞአችሁን ጀምራችኋል። ይህ ጉዞአችሁ ልዩ ነው፤ይህንን ጉዞ ልዩ የሚያደርገው መፅሐፍ ቅዱስን በማወቅ ለማደግ በምታደርጉት የጋለ ፍላጎታችሁ ነው። እግዚአብሔር በቃሉ እውቀት እንዲያበለፅጋችሁ የምታደርጉት ትጋት እጅግ የሚበረታታ ነው። እግዚአብሔር ለህይወታችሁ የሰጠውን የተስፋ ቃል በማወቅ እና ቃሉን በማጥናት ህይወታችሁን የደስታ ህይወት አድርጉት።

ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በምትከታተሉበት ወቅት በእጃችሁ ላይ እንዲኖሩ የሚገባቸው ነገሮ አሉ። እነርሱም፤

1. የዚህ ጥናት መመሪያ መጽሐፍ። "የእግዚአብሔር ፅድቅ የእኛ መቤዤት የሚለው" ማለት ነው።
2. አንድ መጽሐፍ ቅዱስ። መጽሐፍ ቅዱስን በምትገዙበት ወቅት የምትገዙት ትርጉም እነዚህን ያካተተ ቢሆን ይመከራል

   ሀ. በእያንዳንዱ ገፅ ላይ ማጣቀሻ ያለው፤ ማጣቀሻውም በገፁ መካከል ቢሆን ይመረጣል።

   ለ. በመጽሐፍ ቅዱሱ የመጨረሻ ክፍል ጥቅስ ማውጫ ያለው።

   ሐ. እንዲሁ ደግሞ የተለያዩ ታሪካዊ ካርታዎችን ያካተተ ቢሆን መልካም ነው።
3. አንድ እስክርቢቶ ወይንም እርሳስ።
4. አንድ ማስተወሻ መያዣ ደብተር።

   ከላይ በተራ ቁጥር ሁለት ስር እንደተዘረዘረው አንድ ሰው እነዚህን ያሟላ መጽሐፍ ቅዱስ ገዝቶ በእጁ ከያዘ ለጥናቱ በደንብ ተዘጋጅቷል ማለት ነው። እናም ከዚህ በኋላ የሚመጡትን ጥናቶች በሙሉ በመልካም ሁኔታ ማጥናት ይችላል። ሆኖም ግን ይህ ጥናት መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት የምታደርጉት የመጀመሪያ ጥናት ከሆነ፣ ከዚህ አስቀድማችሁ የመጽሐፍ ቅዱስ ዳሰሳ የሚለውን ጥናት መጀመሪያ ብታጠኑት ይበልጥ ይመከራል። ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ዳሰሳ የሚለውን ጥናት ማጥናታችሁ በምታገኙት እውቀት እና በምታደርጉት ጥናት ላይ መተማመን እንድትችሉ ያግዛችኋል።

   ግን እዚህ ጋር ልብ እንድትሉ የምንፈልገው ነገር ቢኖር የመጽሐፍ ቅዱስ ዳሰሳ የሚለውን ጥናት ማጥናታችሁ ይህንን ጥናት በሚገባ እንድትረዱ ያግዛቸኋል እንጂ የግዴታ አለመሆኑን ነው። እናም አንድ ሰው ያንን ጥናት ሳያጠና ይህንን ጥናት ቢጀምር ምንም የሚገጥመው ችግር አይኖርም።

ይህንን ጥናት በምታጠኑበት ወቅት አንድ በጣም የነካችሁ ክፍል ካለ በዚያ ስፍራ መጽሐፍ ቅዱሳችሁ ላይ ምልክት ለማድረግም አትፍሩ። የማጥኛ መጽሐፋችሁ ስለሆነ ከዚያ በኋላ ተመልሳችሁ ለማየት ይረዳችኋል። የራሳችሁ መጽሐፍ ነውና የፈለጋችሁበት ቦታ ላይ ምልክት በማድረግ የፈለጋችሁበት ቦታ ላይ ደግሞ ማስታወሻ በመያዝ እንደሚመቻችሁ አድርጋችሁ አጥኑት። ከፈለጋችሁ ደግሞ ከላይ እንዳልነው የማስታወሻ ደብተር ገዝታችሁ በዚያ ላይ ሃሳባችሁን ሁሉ መፃፍ ትችላላችሁ። በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ማስታወሻችሁን ጻፉበት፣ ጥያቄ የፈጠረባችሁ ነገር ካለም ምልክት አድርጉበት፣ እናም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችሁ ከየት ተነስቶ ወደ የት እየሄደ እንደሆነም ዘግቡበት።

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የተዘጋጀው እያንዳንዳችሁ በግላችሁ ማጥናት እንድትችሉ ተደርጎ ነው። እናም በስርአት ፕሮግራም አውጥታችሁ ካነበባችሁት ያለምንም ችግር ብዙ በረከትን አግኝታችሁበት መጨረስ ትችላላችሁ። እንዲሁም ደግሞ ጥናቱን በምታነቡበት ወቅት አዳዲስ ሃሳቦችን ታገኛላችሁ፣ የእናንተን የማሰላሰል እና የማሰብ አቅም የሚፈትኑ ጥያቄዎችን ታያላችሁ።

ከዚህም ባለፈ የተለያዩ ጓደኞቻችሁን ጋብዛችሁ እነዚህን ጥያቄዎች እየተወያያችሁ ብትሰሩ ብዙ ትጠቀሙበታላችሁ።

ጥናታችሁ የተባረከ እና የደስታ እንዲሆን እንመኝላችኋለን። እግዚአብሔር በቃሉ ሲናገራችሁ ተቀባይ ልቦናንን እንዲሰጣችሁ እንፀልያለን። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እግዚአብሔር አባታችን በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ የገለጠውን ታላቅ ፍቅር የምንረዳበት እና በእርሱ በኩል ያገኘነውን ደስታ እና ሰላም የምንጨብጥበት እንዲሆን ምኞታችን ነው።

## *መግቢያ*

"የእግዚአብሄር ፅድቅ የእኛ መቤዤት" የሚለው የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት በቢሉይ ኪዳን ውስጥ ወደ ተፃፈው የእስራኤል ታሪክ ጥናታችን ፍፃሜ ያመጣናል። በትንቢተ ዮናስ እና በትንቢተ ዳንኤል ውስጥ የተፃፉትን ሶስት ታሪኮችን ትኩረት ሰጥተን እንመለከታለን። እነዚህም ታሪኮች የተለያዩ ታሪካዊ ሰዎች ያስተዋውቁናል። እነርሱም ዮናስ፤ዳንኤል፤ ስድራቅ ፤ሚሳቅ እና አብድናጎ ናቸው። በተጨማሪም የአስቴርን፤የእዝራን እና የነህሚያን መፃህፍት እናጠናቸዋለን። እንደገናም እግዚአብሄር ለህዝቡ ያለውን ታማኝነት እና አላማውን ለመፈፀም በተለያየ ሰዎች ህይወት ውስጥ የሰራቸውን ስራዎች እንመለከታለን።

ይህ ጥናት የሚጀምረው ነቢያት ማን እንደነበሩ፤እንደ እግዚአብሄር ነቢይነታቸው አላማቸው ምን እንደነበረ ዳሰሳ በማድረግ ነው። ከዚያም እነዚህ ታሪካዊ ሰዎች የኖሩበትን እና ያገለገሉበት ታሪካዊ መቼት (መች እና የት እንደነበሩ) እንመለከታለን።

ሀ) ከእስራኤላውያ ቅድመ ምርኮ ታሪክ ወይንም ከምርኮ በፊት ተብሎ በሚታወቀው ታሪካቸው፤ እስራኤል (የሰሜኑ ክፍል) እና ይሁዳ (የደቡቡ ክፍል) ተብሎ የሚታወቁትን በአሶራውያን እና በባብሎናውያ ጦር ሰራዊት በተለያዩ ጊዚያት ከመሸነፋቸው እና ከመማረካቸው በፊት የነበረውን ታሪክ፤

ለ) በባቢሎናውያን እና በፋርሶች አገዛዝ ዘመን የነበውን የይሁዳን 70 የምርኮ አመታት ታሪክ እንዲሁም

ሐ) ንጉስ ቂሮስ እና ንጉስ ዳርዩስ እስራኤላውያ ወደ እየሩሳሌም እንዲመለሱ ከፈቀዱ በኂላ የነበረው የድህረ ምርኮ ታሪክን እንማራለን።

ጥቂት ጊዜ ውሰዱና በመፅሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያዎቹ ገፆች ላይ የመፅሐፍ ቅዱስን መፅሐፍት ማውጫ ገፅ ተመልከቱ። ጥናታችንን ስንቀጥል አንድ የምንገነዘበው ነገር አለ፤ ያም የመፅሐፍ ቅዱስ መፅሐፍት በቅደም ተከተል የተቀመጡት ታሪካዊ ቅደም ተከተላቸውን ተከትለው ሳይሆን በምድብ በምድብ ተከፋለው ነው። ለምሳሌ ያህል አምስቱ የሙሴ መፃህፍት ወይንም የህግ መፃህፍት፤ ከዚያም ከመፅሐፈ ኢያሱ እስከ መፅሐፈ አስቴር ያሉት አስራ ሁለት መፃህፍት የእስራኤልን ታሪክ የያዙ ናቸው። የነቢያት መፅሐፍት የሚጀምሩት ከትንቢተ ኢሳያስ መፅሐፍ ሲሆን እስከ ትንቢተ

ምልክያስ ድረስ ይቀጥላል፡፡ ነብያቱ መልዕክታቸውን የተናገሩት ለተወሰነ ህዝብ እና በተወሰነ ጊዜ እና በታሪካዊ ወቅት ነበር፡፡ እነዚህም ታሪካዊ ከስተቶች በአንደኛ እና ሁለተኛ መፅሐፈ ነገስት፤ በአንደኛ እና ሁለተኛ መፅሐፈ ዜና መዋዕል፤ በመፅሐፈ አስቴር፤በመፅሐፈ እዝራ እና በመፅሐፈ ነህምያ ውስጥ ተፅፈው ይገኛሉ፡፡

የመፅሐፍ ቅዱስን ታሪካዊ ካርታዎችን ስታጠኑ እንዴት ሰዎች ከተስፋይቱ ምድር ወደ ምርኮ አገር ምርኮኛ ሆነው እንደተጓዙ ትረዳችሁ፡፡ ይህንን ጉዞ ማጥናት አስፈላጊ የሚሆንበት ምክያት አሁን እንደአለንበት ዘመን (21ኛው ክፍለ ዘመን) አይነት ፈጣን እና ምቹ የሆነ የመጓጓዣ ቴክኖሎጂ በሌለበት በዚያን ወቅት ረጅሙን የምድረ በዳ መንገድ በእግራቸው መጓዛቸውን እንድንገነዘብ ስለሚያደርግ ነው፡፡

ለጥናቱ ተዘጋጁ ! በመፅሐፍ ቅዱስ ጥናቱም ተደሰቱ፡፡ ይህንን ጥናት ስታካሂዱ እና ወደ ትግበራ ስትመጡ አዳዲስ መፅሐፍ ቅዱሳዊ ሃሳቦችን፤ትምህርቶችን፤ታሪኮችን እና አስተሳሰቦችን ለመረዳት እና የራሳችሁ ለማድረግ እንዲሁም በስራ ላይ ለማዋል ጥረት አድርጉ፡፡ ጌታ ለልባችሁ የሚናገርበትን ስፍራ አስተውሉ፡፡ ዮናስ የአሳ ነባሪ ሆድ ውስጥ ሆኖ ፀለየ፤ ዳንኤል ደግሞ የአንበሳ ዋሻ ውስጥ ሆኖ ፀለየ፡፡ ስድራቅ ፤ሚሳቅ እና አብድናጎ እስራታቸው ተፈትቶ በእቶን እሳት ውስጥ ተመላለሱ፤ እንዲሁም አስቴር በንጉሱ ፊት በድፍረት ቆመች፡፡ ምናልባትም ከበርካታ የእስር እና የምርኮ አመታት በኋላ ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመመለስ ከተሰባሰቡት ሰዎች መካከል ልትሆኑ ትችላላችሁ፡፡ ምንአልባትም ወደፊት ሊሆን የሚችለውን ነገር ካለማወቃችሁ የተነሳ በፍርሃት ውስጥ ልትሆኑ ትችላላችሁ፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ አልፋችሁ የማታውቁ ከሆነ አካባቢያችሁን ማስተዋልን አትርሱ፡፡ እናንተ የምትጓዙት ከብዙ ሰዎች ጋር ነው፡፡ እኛ የምንጓዘው ያለፈውን ታሪካችንን የተቤዠው እና ለወደፊቱ ህይወታችን ተስፋን ከሰጠን ከአምላካችን ከእግዚአብሔር ጋር ነው፡፡

ጥናታችንን ከመጀመራችን በፊት መታወቅ የሚገባው ነገር... መቤዠት ማለት አንድን ነገር ወይም አንድን ሰው እንደገና መግዛት እና የራስ ማድረግ ማለት ነው፡፡ መቤዠት አስፈላጊው ክፍያ ስለተፈፀመ ከተያዙበት ነገር መለቀቅ ወይንም ነፃ መውጣት ነው፡፡

መቤዠትን የአገኘ ሰው አርነት የወጣ ወይንም ነፃ የሆነ ሰው ነው፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ እግዚአብሄር ህዝቡን መቤዠቱን እናጠናለን፡፡

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ ምድር ከአራት መቶ አመታት በላይ ከሆነ የባርነት ኑሮ እና ህይወት ተቤዣቸው (ዘፀአት 1 - 14)፡፡ አሁን ደግሞ እስራኤላውያን ከምርኮ አገር ሲመለሱ እና እግዚአብሔር እንደገና በተስፋይቱ ምድር ሲያቋቅማቸው እንመለከታለን፡፡

መፅሐፍ ቅዱስ የሚነገረን እግዚአብሔር እኛን ሲቤዠን እና ነፃ ሲያወጣን በፊቱ በፅድቅ፤ ይቅር የተባለ፤ የሚወደድ እና የዘላለም ህይወት ወራሾች እንድንሆን ነው፡፡ እግዚአብሔር ለህዝቡ ለእስራኤል ያደረገውን የመቤዠት ስራ ተመልከቱ፤ ጥናታችሁንም ቅጥሉ፡፡

# ክፍል አንድ

# እግዚአብሔር ሲመለከት … እግዚአብሔር ተወ

# ትንቢተ ዮናስ 1 - 4 — የዮናስ ታሪክ

**የክፍል አንድ ቅኝት**

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 1፡ ትንቢተ ዮናስ

- የነቢዩ ስራ
- ታሪካዊ ዳራ
- የእግዚአብሔር ትዕዛዝ
- የዮናስ ምላሽ
- በአሳው ሆድ ውስጥ
- ጉዞ ወደ ነኔዌ
- የእግዚአብሔር ርህራሄ እና ምህረት
- ግን

## መግቢያ

እግዚአብሔር ለሚሰጠን ትዕዛዝ የምንሰጠው ምላሽ ሁልጊዜ ከመታዘዝ የሆነ ምላሽ አይደለም፡፡ ዮናስ ለእግዚአብሔር "እሺ" ማለትን አልፈለገም፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ እግዚአብሔር ዮናስን ምን እንደጠየቀው እና የዮናስ ምላሽ ምን እንደ ነበር አስተውሉ፡፡ የዮናስን አደገኛ የሆነ አለመታዘዝ እግዚአብሔር ምን አደረገው? የዮናስ አለመታዘዝ እንዴት አድርጎ ነው በአካባቢው ባሉት ሰዎች ላይ ተፅዕኖ የሚያመው? እግዚአብሔር በዮናስ ተስፋ ቆረጠ? እግዚአብሔር በእኛ ተስፋ ይቆርጣል?

ትንቢተ ዮናስ ስታጠኑ "ግን" የሚለውን ቃል ስታገኙ አክብቡት ወይንም አቅልሙት፡፡ መፅሐፉን አንብባችሁ ስትጨርሱ "ግን" የሚለው ቃል ምን ያህል እንደተደጋገመ አስተውሉ፡፡ ጊዜ ውሰዱ እና በዮናስ ህይወት ውስጥ የተለያዩ "ግን" የተባሉትን ጉዳዮችን አስተያየት ስጡባቸው፡፡ በህይወታችሁ ውስጥ "ግን" የሚለው አባባል የሚያመባችሁን ልዩነትን አጢኑ፡፡

ትንቢተ ዮናስ 2:10 እንዲህ ይላል፤ "እኔ ግን በምስጋና ቃል እሠዋልሃለሁ የተሳልሁትንም እከፍላለሁ፡፡ ደኅንነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው!" የእግዚአብሔር ፍቅር ከዮናስ አለመታዘዝ እና አመፅ ይበልጣል፡፡ እግዚአብሔር ለዮናስ ንስሃ የሚገባ ልብን፤ በውዳሴ እና በምስጋና ለጌታ ምላሽን የሚሰጥን ልብ ሰጠው፤ የእግዚአብሄር ተስፋ በራሱ ፅኑ ፍቅር ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

## ክፍል 1

### መግቢያ

የቢሉይ ኪዳን መፃህፍት የሆኑት ከትንቢተ ኢሳያስ እስከ ትንቢተ ሚልክያስ ድረስ ያሉት መፃህፍት የተፃፉት በነቢያት ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች በእግዚአብሔር መንፈስ የተሞሉ፤ ለሰዎች፡ ለነገስታት እና ለካህናት የጌታን ቃል ያስተላለፉ ወይንም የተናገሩ ናቸው፡፡ ከዚህ በፊት በነበረው "የእግዚአብሔር ምህረት የእኛ ድነት" በሚለው የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናታችን ስለነገስታት እና ስለተወሰኑ ነብያት በአንደኛ እና ሁለተኛ መፅሐፈ ነገስት እንዲሁም በአንደኛ እና ሁለተኛ ዜና መዋልዕ ውስጥ ተመልክተናል፡፡ ጥናቱ እንደ ኢሳያስ እና ኤርሚያስ ሳይሆን ኤልያስ እና ኤልሳዕ የተባሉትን ሁለት ለየት ያሉትን ነቢያቶችን ጥናቱ አጠቃልሏል፡፡

### አስተምሮ

ይህ ጊዜ ነቢያት ማን እንደነበሩ እና እንደ ነቢይ አላማቸው ምን እንደነበረ ለመከለስ መልካም አጋጣሚ ነው፡፡ ምንም እንኳን ህዝቡ የእርሱን አመራር እና አገዛዝ ከህይወታቸው ለማስወገድ ጣኦታትን በማምለክ እያመነዘሩና ክፉ ማድረግን ተያይዘው ቢቀጥሉበትም እግዚአብሔር ግን ያለማቋረጥ በፅኑ ፍቅሩ ይወዳቸው ነበር፡፡ የእርሱ ዋናው ፍላጎት የእርሱ ከሆኑት እና እርሱ ከመረጣቸው ህዝቦች ጋር ግንኙነቱን አጥብቆ መቀጠል ነው፡፡ ነቢያት ዋናው ተግባራቸው እግዚአብሔር ህዝቡ ወደ እርሱ እንዲመለሱ በሚያደርገው ጥሪ የእርሱ ድምፅ ሆነው ማገልገል ነው፡፡

እነዚህ መልዕክተኞች በእግዚአብሔር የተመረጡ ሲሆኑ ዋናው ተግባራቸው እስራኤላውያን በህይወታቸው ለመከተል ከመረጡት ክፉ መንገድ የተነሳ የፍርድን ቃል ማወጅ ነበር፡፡ እነርሱ ጌታን ትተው "በዓልን" እና የፍቅር አምላክ የሚሏትን "አስታሮትን" ወድቀው በመስገድ ያመልኳቸው ነበር፡፡ የእነርሱ የባዕድ አምልኮ የጥንቆላን፤መተትን፤ሟርትን መለማመድን፤የተለያዩ መናፍስትን ማምለክን እና ሰዎችን በእሳት ውስጥ እያሳለፉ መስዋዕት አድርጎ ማቅረብን ያጠቃለለ ነበር፡፡

እግዚአብሔር ህዝቡ ከክፉ መንገዳቸው እንዲመለሱ እና ከእርሱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንዲያድሱ የምህረቱን ተስፋ እየሰጠ በነቢያቱ በኩል ጥሪውን ያስተላልፍ ነበር። በዋናነት ነቢያቱ የእግዚአብሔርን ህዝብ የተሳሳተ አቅጣጫቸውን እንዲቀይሩ እንዲሁም ሊዳኛቸው እና ሊቤዣቸው ወደሚመጣው ፃዲቅ ወደ ሆነው እየሱስ ክርስቶስ ያመላክቱ ነበር (ትንቢተ ኤርሚያስ 23:5-6) ።

በዚህ ጥናት ውስጥ ስለነቢያት ሶስት ዓይነት ስራዎች እንመለከታለን። 1)የእግዚአብሔርን ፍርድ ማወጅ 2) የእግዚአብሄርን ህዝብ ለንስሐ መጥራት - ሰዎች ክፉ ስራቸውን በመተው ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ መጥራት፤ እንዲሁም 3) የእግዚአብሔርን ምህረት እና ከህዝቡ ጋር ያለውን ግንኙነት ለማደስ የሰጠውን ተስፋ ማወጅ ናቸው።

### *ታሪካዊ ዳራ ወይም አውድ*

ቀጣዩ ከባድ ስራችን የሚሆነው በታሪክ ውስጥ በነገስታቱ የተከናወኑትን ተግባራት እና ነቢያቱም ለነገስታቱ ያወጁዋቸውን የእግዚአብሔርን የፍርድ ታሪካዊ አውዱን ጠብቆ በቅደም ተከተል መረዳቱ ነው። በሁለተኛ ዜና መዋልዕ 36:15-21 ባለው ክፍል ውስጥ የባቢሎን ንጉስ የሆነው ናቡክደናፆር እየሩሳሌምን እንዳፈራረሳት እና ከእልቂቱ የተረፉትን ምርኮኛ አድረጓቸው ወደ ባቢሎን እንደወሰዳቸው እንመለከታለን። እነዚህ ቅሬታዎች በባቢሎን አገር እንደ ባሪያዎች እና አገልጋዮች ሆነው ለሰባ አመታ ኖሩ። በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ የፋርስ ንጉስ የባቢሎውያንን ንጉስ አሸንፎት ወደ ስልጣን መጣ።

### *<u>ቅድመ ምርኮ</u>*

በቅድመ ምርኮ አመታት እስራኤላውያ በይሁዳ እና በእስራኤል ውስጥ ይኖሩ ነበር። ኢሳያስ እና ኤርሚያስ ከብዙ ነቢያት መካከል በቅድመ ምርኮ በእየሩሳሌም እና በይሁዳ ለሚኖሩ ሰዎች ትንቢትን ተናግረዋል።

1. በትንቢተ ኢሳያስ 5፡ 4-6 ውስጥ ያለውን የኢሳያስን ማስጠንቀቂያ አንብቡት። ከቁጥር 8-23 ያሉትን ስታነቡ “ወዮላቸው” የሚለውን ቃል አስምሩበት። ኢሳያስ ምዕራፍ 5 ለእራኤላውያ ነቢዩ የሰጣቸው ማስጠንቀቂያዎች ምሳሌ ነው። ይህ ምዕራፍ የወዮላችሁ እና የፍርድ ቃላት የሚገኙበት ምዕራፍ ነው።
   በቁጥር 7 ስለ ወይኑ እርሻ ኢሳያስ የሚናገረው ስለማን ወይንም ማንን እያሰበ ነው?
   ___________________________________________________________

ሀ. ጌታን በሰራው ስራ ላይ በአላከበሩት ሰዎች ላይ የተነገረው ፍርድ ምንድነው (ቁጥር 11-15)? ____________________________________________

____________________________________________

ለ. ራሳቸውን ከኃጢአት፤ከክፋት እና ሰዎችን ከማሳት ጋር በአቆራኙት እንዲሁም መልካሙን ክፉ፤ክፉውን መልካም በሚሉ፤ ራሳቸውን ጠቢባን በአደረጉ፤ የወይን ጠጅን እየጠጡ በሚሰክሩ ፤ በደለኛውን ችላ በሚሉ እና ፍትህን በሚያጓድሉት ላይ የተነገረው ማስጠንቀቂያ ምንድነው (ቁጥር 18-25)?

____________________________________________

____________________________________________

2. በኤርሚያስ 3:6-14 ላይ ያለውን ያንብቡት እና "ከዳተኛይቱ" (የእስራኤል መንግስት) የሚለውን እና "አታላይ" (የይሁዳ መንግስት) የሚሉትን ቃላት አስምሩባቸው፡፡ ኤርሚያስ ፤የሚናገረው ለእግዚአብሔር ታማኝ ስለአልሆነው የእግዚአብሔር ህዝብ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ህዝብ ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን ሲገባቸው እነርሱ ግን ጣኦታትን በማምለክ፤ ጠማማነትን እና ክፋትን በመምረጥ አመነዘሩ፡፡

ሀ. ኤርሚያስ ከቁጥር 6-10 ባለው ውስጥ ያስረዳው ስዕላዊ ገለፃ ስለምንድነው?

____________________________________________

____________________________________________

ለ. በቁጥር 12 ላይ እግዚአብሔር ስለራሱ ምን አለ?

____________________________________________

____________________________________________

ሐ. ከቁጥር 12 -14 ባለው ክፍል ውስጥ በነቢዩ በኩል ለከዳይተኛይቱ እስራኤል ምን የሚል መልዕክትን እግዚአብሔር ላከ?

"ሂድና ይህን ቃል ________________________፥ እንዲህም በል፡፡ ________________________፥ ተመለሽ፥ ይላል እግዚአብሔር ________________________________ በእናንተ ላይ ፊቴን አላደርግም፥ ይላል ______________________፦"(ቁጥር 12 እና 14)፡፡

መ. እግዚአብሔር በቁጥር 13 ኃጢአታቸውን______________________እንዲያደርጉ ጥሪን አቀረበላቸው፡፡

ሐ. እነርሱስ ምን አደረጉ (ቁጥር 13)?

______________________________________________________________________

_______________________________________________________

i. በአምላክሽ በእግዚአብሔር ላይ ________________________________

ii. ____________________________________________ለእንግዶች እንደ ዘረጋሽ

iii. ቃሌንም እንዳልሰማሽ ____________________ ይላል እግዚአብሔር።

ኢሳያስ እና ኤርሚያስ ለእስራኤል እና ለይሁዳ ህዝብ እና ነገስታት ማስጠንቀቂያን ከእግዚአብሔር ዘንድ የተናገሩ ነቢያት ምሳሌዎች ናቸው። የሰሜኑ መንግስት፤ እስራኤል በጠላት ለመደምሰስ የመጀመሪያው ነበር። በንጉስ ሰልምናሶር እየተመሩ አሶራውያን እስራኤልን በቁጥጥራቸው ስር አደረጉ። ትንቢተ ዮናስ የተፃፈው የእስራኤል መንግስት ከመደምሰሱ በፊት ነበር።

**<u>የምርኮ ወቅት</u>**

የምርኮ ወቅት የሚባለው እስራኤላውያን በንጉስ ናቡከደነፆር በምትመራው ባቢሎን ውስጥ ተማርከው የኖሩበትን አመታት የሚያመለክት ነው። ትንቢተ ዳንኤል በተወሰነ ደረጃ ህዝቡ እንዴት በንጉስ ናቡከደነፆር በምትመራው ባቢሎን ውስጥ ይኖር እንደነበረ ይዘግባል። የይሁዳ ሰዎች በምርኮ ውስጥ የነበሩበትን ታሪክ የምናጠናው ትንቢተ ዳንኤልን እና መፅሐፈ አስቴርን በማየት ነው። የምርኮው አመታት ያበቃው በ539 ዓመተ ዓለም ወይም ከክርስቶስ ልደት በፊት የፋርስ ንጉስ ቂሮስ ባቢሎንን በአሸነፈበት ወቅት ነበር። ምርኮኞቹ ግን ወደ እየሩሳሌም የተመለሱት ለበርካታ አመታት በቆየ ተከታታይ በሆነ በቡድን በቡድን ሆነው በመመለስ እንቅስቃሴ ነበር።

**<u>ድህረ ምርኮ</u>**

ድህረ ምርኮ የሚባሉት አመታት እስራኤላውያን በፋርስ ንጉሶች በቂሮስ እና አርጤክስስ ዘመን ወደ እየሩሳሌም መመለስ የጀመሩትን አመታት የሚያመለክት ነው። የመፅሐፈ እዝራ እና ነህምያ ታሪኮች የተፈፀሙት እስራኤላውያን ከምርኮ በኋላ ወደ ተስፋይቱ ምድር ከተመለሱ እና በምድራቸው መኖር ከጀመሩ  በኋላ ነው።

በቢሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኙት መፅሐፎች ከዚህ በፊት እንደገለፅነው በታሪካዊ ቅደም ተከተላቸው የተቀመጡ አይደሉም፡፡ “የእግዚአብሔር ፅድቅ የእኛ መበገፔት” የሚለው ጥናት የእራኤላውያንን ታሪክን በሚከተለው ታሪኮች መሰረት ይነግረናል፡፡

1. ዮናስ ወደ ነነዌ መላክ
2. ዳንኤል እና የአንበሳዎች ጉድጓድ
3. ስድራቅ፤ ሚሳቅ እና አብድናጎ እንዲሁም የእቶኑ እሳት
4. አስቴር የፋርስ ንግስት
5. መሪው ዘሩባቤል እና ህግ ሰጪው እዝራ
6. የግንባታ ሰው የሆነው ነህምያ

**የማበረታቻ ቃላት፡-**

የተለያየ ገፀ - ባህሪያትን በያዙ የተለያዩ ስሞች ፤ በርካታ መሐፍት፤ወይንም በዘመናቱ ቅደም ተከተሎች ብዙም አትደነቁ፡፡ በክፍል አንድ ውስጥ በኢሳያስ እና ኤርሚያስ ስራዎች ስለነቢያት ተግባራት ተዋውቃችኋል፡፡ የቅድመ ምርኮን፤ በባብሎን እና በፋርስ የነበረውን የምርኮ አመታትን እና የድህረ - ምርኮን ታሪካዊ አመታትን በአጭሩ ተመልክታችኋል፡፡ በተጨማሪም በጥናቱ ውስጥ የተካተቱን ታሪኮች በዝርዝር ተመልክታችኋል፡፡ ስለዚህ ቀጥለን የትንቢተ ዮናስ ጥናታችንን እንቀጥላለን፡፡

## <u>ትምህርት 2</u>

**የቤት ስራ**

ትንቢተ ዮናስ አራት ምዕራፎች ያሉት መፅሐፍ ነው፡፡ እነዚህን መፅሐፎች በአንድ ጊዜ አንብቧቸው፡፡ ስለ ዮናስ እና አሳ ነባሪው ታሪክ ደጋግማችሁ አንብቡ፡፡ ክፍሉን ስታነቡ ትኩረታችሁን የሳበውን ቃላት አስምሩበት፡፡

**መልመጃ**:

1. ትንቢተ ዮናስ 1:1 የጌታ ቃል ወደ ________________ ______________የልጅ እንዲህ ሲል መጣ፡፡ ከመፅሐፍ ቅዱስ 2 ነገስት 14፡ 23-25 አውጡና ትንቢተ ዮናስ 1:1 ካለው ክፍል ጋር አመሳክሩ፡፡

ሀ. በቁጥር 23 ላይ የምንማረው ነገር ስለ እስራኤል ንጉስ ኢዩርብአም ሁለተኛ ነው፡፡ ስለዚህ ንጉስ በቁጥር 24 ላይ የተነገረን ነገር ምንድነው 24?

______________________________________________

ለ. በቁጥር 25 ላይ የጌታን ቃል ለእርሱ የተናገረው ነቢይ ማን ይባላል ?

______________________________________________

ሐ. ነቢዩ የመጣው በስተሰሜን የእስራኤል ከተማ ከሆነው ከሐማት ከጋትሔፌር ነው፡፡

2. በትንቢተ ዮናስ 1፡2 የተጠቀሰው ለነቢዩ ዮናስ የመጣለት የጌታ ቃል ምን የሚል ነው 1:2? ______________________________________________

______________________________________________

ይህን ታላቅ ከተማ በመፅሐፍ ቅዱሳችሁ መጨረሻ አካባቢ በሚገኘው ካርታ ላይ አመላክቱ፡፡ ይህ ከተማ የት ነው የሚገኘው?

______________________________________________

3. በቁጥር 3 መሰረት ዮናስ የሰጠው ምላሽ ምን ነበር?

______________________________________________

**አስተምሮ**

ዮናስ ወደ ነነዌ እንዲሄድ በእግዚአብሔር ተነገረው፡፡ ይሁን እንጂ እርሱ ከጌታ ሸሸ፡፡ ዮናስ ለጌታ ትዕዛዝ የሰጠውን ምላሽ በደንብ ለመረዳት ስለ ታላቋ ከተማ ነነዌ ማወቅ አለብን፡፡ ነነዌ የአሶራውያን መንግስት ዋና ከተማ ስትሆን ንጉስዋ ደግሞ ስልምናሶር ሲሆን በዘመኑ የነበረው የእስራኤል ንጉስ ደግሞ ሆሴዕ ነው፡፡ ንጉስ ስልምናሶር እስራኤልን ወርሮ በመያዝ እስራኤላውያንን ምርኮኛ አድርጎ ወሰዳቸው (2 ነገስት 17)፡፡ ንጉስ ስልምናሶር እስራኤልን የቅኝ ግዛቱ በማድረግ ሊያስገብራቸው ይፈልጋል፡፡

የአሶራውያን ወረራ የማይቀር ጉዳይ ስለሆነ ጌታ ነቢዩ ዮናስን እንዲህ አለው “ወደ ታላቂቱ ከተማ ወደነነዌ ሂድና እንዲህ በላቸው…” እግዚአብሄር እስራኤልን ለመውረር እየተዘጋጀች ወደምትገኘው አገር ዋና ከተማ ዮናስን እየላከው ነው፡፡ በዚህን ጊዜ ነቢዩ ዮናስ ምን ማድረግ አለበት? እግዚአብሄርስ ምን እያሰበ ነው? ዮናስ ምን እንዲያደርግ ነው እግዚአብሄር እየጠየቀው ያለው፤ተናግሮ መሞት!? ምርኮኛ መሆን? ባሪያ መሆንን? ወይንም የራሱ የሆነውን የጅል ተግባር የሆነውን ሃሳቡን መፈፀም?

የነነዌ ከተማ ከእግዚአብሄር የንስሐ እድል የተሰጣት ለምንድነው? ዮናስ አሶራውያን ወይንም የነነዌ ሰዎች ከእርሱ የተለዩ ህዝብ ስለሆኑ ነው መልዕክቱን ላለማድረስ በተቃራኒ አቅጣጫ የሄደው? እነርሱን እንደክፉ ጠላት መቁጠር ነበረበት?

እነዚህ ጉዳዮች የትንቢተ ዮናስን መፅሐፍ እንድንረዳ ይጠቅሙናል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ የጌታ ቃል ወደ ነቢዩ ዮናስ የመጡበትን ምክንያት እንድናውቅ ያግዙናል፡፡

**የማሰላሰል ጥያቄዎች**

1. ወደ አንድ ስፍራ እንዲሄድ እግዚአብሄር ቢልከኝ እሄዳለሁ? ህይወቴን አደጋ ላይ ሊጥል ወደሚችል ስፍራ እግዚአብሄር ሂድ ቢለኝ እሄዳለሁ? ወደ ተላኩበት ስፍራ እንዲሄድ ወይንም እንዳልሄድ የሚያደርጉኝ ነገሮች ምንድን ናቸው?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

2. እራሴን እንደዮናስ አድርጌ ልቆጥር እችላለሁ? ወደ ተላኩበት ስፍራ እንዳልሄድ የሚያደርጉኝ ነገሮች ምንድን ናቸው?

______________________________________________

______________________________________________

<u>**ክፍል 3**</u>

***መልመጃ***

1. ይሁን እንጂ ዮናስ ሸሽቶ ወደ ______________________ አቀና (ቁጥር 3)፡፡ ተርሴስ የት እንደምትገኝ በትክክል የሚያውቅ ሰው የለም፤ ይሁን እንጂ ወደ ምዕራብ አውሮፓ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፤ ነገር ግን መሄድ የነበረበት በምስራቅ አቅጣጫ ወደነነዌ መሆን ነበረበት ፡፡ እርሱ ግን በግልፅ የተጓዘው በተቃራኒ አቅጣጫ ነበር፡፡
2. በካርታ ላይ ዛብሎን የሚለውን ክልል ፈልጉ እና በኢዮጴም ላይ ምልክት አድርጉበት፡፡ ዮናስም ከኢዮጴም ተነስቶ በመርከብ ወደ ተርሴስ ጉዞውን ቀጠለ፡፡ በቁጥር 3 ላይ በተጠቀሰው መሰረት ወደተርሴስ የሄደበት ምክንያት ምንድነው?

______________________________________________

______________________________________________

3. በመርከቢቱ ላይ የደረሰው ነገር በራሳችሁ አገላልፅ ግለፁት

____________________________________________________________

____________________________________________________________

___________________________________________________________

ዮናስ ወዴት ሄደ? ምንስ እያደረገ ነበር?

__________________________________________________________

4. የመርከቢቱ ካፒቴን በጣም ተደናቅጧል። ካፒቴኑ ዮናስ ምን እንዲያደርግ ነው የፈለገው(ቁጥር 6)? ____________________________________________

____________________________________________________________

5. የመርከበኞቹስ መፍትሄ ምን ነበር (ቁጥር 7)?

____________________________________________________________

6. ውጤቱስ ምን ነበር?

___________________________________________________________

7. መርከበኞቹ በፍጥነት ከመንገደኞቹ ጋር ተዋወቁ። የጠየቁትን ጥያቄዎች እስኪ ገምቷቸው። ለእነርሱ ጥያቄዎች የዮናስ መልስ ምን ነበር (ቁጥር 8-9)?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

8. መርከበኞቹ ዮናስ ከጌታ ሸሽቶ እየሄደ እንደሆነ ተረድተዋል፤ማወቅ የፈለጉት ነገር ለምን ከአምላኩ እየሸሸ እንደሆነ ነው። እርሱም ለጠየቁት ጥያቄ ሲመልስላቸው “እኔ ዕብራዊ ነኝ ባሕሩንና የብሱን የፈጠረውን የሰማይን አምላክ እግዚአብሔርን እመልካለሁ አላቸው።” እነርሱ ምንን ማወቅ ነው ፈለጉ (ቁጥር 10)?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

9. ከዚህም በኋላ የዚህን አምላክ ቁጣ ሊያስታግስ የሚችል ነገር ምን እንደሆነ ማወቅ ፈልገዋል። ዮናስን “____________________________________________”
ብለው ጠየቁት (ቁጥር 11)።
በቁጥር 11 ላይ ለተጠየቀው ጥያቄ የዮናስ ምልስ ምን ነበር (ቁጥር 12)?

____________________________________________________________

10. ዮናስ በተሳሳተ መንገድ ላይ እንደሆነ አውቋል። በመርከቢቱ ላይ የተፈጠረው ችግር በእርሱ ምክንያት እንደሆነ በሚገባ ተረድቷል፤ ስለዚህ መፍትሄው ደግሞ እርሱን ወደሚናወጠው ባህር እንዲወረውሩት ማድረግ ነበር፤ በዚህን ጊዜ መርከበኞቹ ምን አደረጉ? ______________________________

11. ይሁን እንጂ ታላቁ ማዕበል በርትቷል። መርከበኞቹ ወደመሬት እየቀዘፉ መሄድ አልቻሉም። በቁጥር 14 ላይ ወደ ጌታ ጮሁ። የፀሎታቸው ዋና ሃሳብ ምን ነበር?

______________________________

______________________________

12. በቁጥር 15 እና 16 ላይ ምን ሆነ ይለናል?

ሀ. በዮናስ ላይ?

______________________________

______________________________

ለ. በባህሩ ላይ?

______________________________

ሐ. በመርከበኞቹ ላይ?

______________________________

13. እግዚአብሄርስ ምን አደረገ ቁጥር 17?

______________________________

"ዮናስም______________________________

______________________________"

**ማሰላሰል**

እስኪ ጥቂት ጊዜ ወስደን በምዕራፍ አንድ ላይ የተፈፀሙትን ነገሮች እናሰላስላቸው።

1. ዮናስ ከሚያመልከው አምላክ ሸሽቶ መሄዱ መልካም ይመስላችኋል (ቁጥር 9)? ምን አይነት ሃሳቦች ወደአዕምሮአችሁ ይመጣሉ? መቼ ነው ከፈጠራችሁ አምላክ ፈቃድ ስትሸሹ ራሳችሁን ያገኛችሁት?

______________________________

______________________________

2. ዮናስ ለሚያመልከው እውነተኛው አምላክ ታዛዥ አይደለም፤ መርከበኞቹ ግን ለአማልክቶቻቸው ታዛዦች ነበሩ። መርከበኞቹ በዮናስ አለመታዘዝ ምክንያት የመጣባቸውን የእግዚአብሔርን ቁጣ ለማብረድ ምን ብለው እንደተናገሩ እና ምን እንዳደረጉ ከልሱ

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

3. ምንም እንኳን ዮናስ ከእግዚአብሄር ቢሸሽም እግዚአብሄርስ ምን ያህል ከእርሱ ርቆ ነበር?

ሀ. በቁጥር 4 ላይ ማዕበልን የሚያስነሳ ታላቅ ንፋስን የላከው ማነው?

____________________________________________________________

ለ. በቁጥር 17 ላይ ትልቁን ዓሳ ያዘጋጀው ማነው?

____________________________________________________________

2.ዮናስ ደግሞ በአልጠበቀው ነገር ሆድ ውስጥ ራሱን አገኘው።

ሀ.ቁጥር 5 እርሱ __________________________ ውስጥ እንደሆነ ይነግረናል።

ለ.ቁጥር 15 እርሱ __________________________ውስጥ እንደሆነ ይነግረናል።

ሐ.ቁጥር 17 እርሱ __________________________ውስጥ እንደሆነ ይነግረናል።

2. እነዚህ ስፍራዎች ለዮናስ ምንድን ናቸው? እነዚህ ቦታዎች ዮናስን ለመያዝ እና ለመደበቅ ብቁ ናቸው። ዮናስ ምን የሚፈለግ ይመስላችኋል? መደበቂያ ስፍራ? መደበቅ የሚችል መስሎት ነበር?

______________________________________________________________

3. እግዚአብሄር የሚወዳቸውን ከየት ነው ያገኛቸው?

ሀ. በኦሪት ዘፍጥረት 3 ላይ አዳም እና ሔዋን ኃጢአትን ሰሩ፤ እግዚአብሄርም ግን ወደ ተሸሸጉበት ስፍራ ሊፈልጋቸው ሄደ። እርሱ የት እንዳገኛቸው አስታውሱ (ዘፍጥረት 3:8-9) __________________________________________

ለ. እግዚአብሄር ቃየንን ከየት አገኘው (ዘፍጥረት 4)?

______________________________________________________________

ሐ. እግዚአብሄር ሎጥን ከየት አገኘው (ዘፍጥረት 19)?

______________________________________________________________

መ. እግዚአብሄር ሙሴን ከየት አገኘው (ዘፀአት 3) ?

ሠ. እግዚአብሄር ሩትን ከየት አገኛት (መፅሐፈ ሩት 1)

______________________________________________

ረ. እግዚአብሄር ሳሙኤልን ከየት አገኘው (1 ሣሙኤል 3)

______________________________________________

ሰ. እግዚአብሄር ዳዊትን ከየት አገኘው (1 ሣሙኤል 16)?

______________________________________________

4. እግዚአብሄር አርነት የሚያወጣው አምላክ እንደሆነ ዮናስ ያውቅ ነበር፡፡. በትንቢተ ዮናስ 2፡6 ላይ ዮናስ የተናገረው ነገር ምን ነበር?

______________________________________________

______________________________________________

**ትግበራ**

1. ማንም ሰው እንዳያገኛችሁ በማሰብ የተደበቃችሁበትን ጊዜ ታስታውሳላችሁ?__________

______________________________________________

______________________________________________

2. ወዴት ነው ለመደበቅ የሄዳችሁት? የመደበቂያ ስፍራዎቻችሁ የት ናቸው?

______________________________________________

______________________________________________

3. ትንቢተ ኤርሚያስ 23፡23-24 አንብቡ

ሀ. እግዚአብሄር የሚጠይቀው የመጀመሪያው ጥያቄ ምንድነው?

______________________________________________

ለ. ቀጣዩስ ጥያቄ ምድነው?

______________________________________________

ሐ. መጨረሻ ላይ እግዚአብሄር ምን ጠየቀ?

______________________________________________

4. እነዚህ ጥያቄዎች በሁሉም ስፍራ ስለሚገኘው አምላክ ምን ያህል መረዳቴን ይጨምርልኛል?

______________________________________________

**ጠንከር ያለ ጥያቄ**

ዘመዶቼን እና አብረውኝ የሚሰሩ ሰዎችን ሳገኛቸው...

1. የእግዚአብሄር መገኘት ሰላምን እና እረፍትን እንደሰጠኝ እንዴት ልገልፅላቸው እችላለሁ? እነርሱም ከተደበቁበት ስፍራ ወጥተው እንዴት የእግዚአብሄርን ሰላም እና የእርሱን እንክብካቤ ሊያገኙ እንደሚችሉ ልነግራቸው እችላለሁ?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

2. ምንስ ብዬ ልናገራቸው እችላለሁ?

_______________________________________________

_______________________________________________

**ፀሎት**

እግዚአብሄር እኔን ተጠቅሞ ሌሎችን እንዲያገኛቸው

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

**ማስታወስ**

እኔ ከእግዚአብሄር አምላኬ ተደብቄ ከእርሱ መለየት አለመቻሌን ማወቄ ትልቅ መፅናናትን ይሰጠኛል። እግዚአብሄር እራሱን ከሰዎች አይደብቅም፤ ሰዎችም ከእርሱ መደበቅ አይችሉም። እርሱ ሰማያትን እና ምድርን የፈጠረ አምላ ነው። እኔንም የፈጠረው እርሱ ነው። እኔ የእርሱ እርሱም የእኔ ስለሆነ ከእርሱ ማምለጥ አልችልም (መዝሙር 139:7-10)። እርሱን ፈልጌ የማላገኝበት ቦታ የለም። እርሱ በሁሉም ስፍራ ከእኔ ጋር አለ። በሮሜ 8:38-39 ላይ ያሉትን ጥቅሶች በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ፃፏቸው እና በደንብ አጥኗቸው። ስለእነዚህ ጥቅሶች ያላችሁን መረዳት አብራሩ።

_______________________________________________

_______________________________________________

## ክፍል 4

**ትግበራ**:

1. ይህ ጥናት ራሳችንን እንድንመለከት ያሳስቡናል። በእውነተኛው አምላክ የማይታመኑ ሰዎች እምነታቸውን የሚያደርጉት ማዳን በማይችሉ ጣኦታት ላይ ነው። እኛስ ዛሬ ጥቅም የሌላቸው ነገር ግን የምንታመንባቸው ነገሮች ምንድናቸው?

____________________________________________

____________________________________________

2. እምነታችንን እና ተስፋችንን በሰዎች እና በነገሮች ላይ ስናደርግ የሚጠብቀን ቅጣት ምን ሊሆን ይችላል?

____________________________________________

3. እምነታችንን እና ተስፋችንን በእግዚአብሄር ላይ ወይንም ምንም ጥቅም በሌላቸው እና ጊዜያዊ በሆኑ በሰዎች እና በቁሳቁሶች ላይ የማድረግ ምርጫ አለን። ይሁን እንጂ ሁለቱንም በአንድ ጊዜ ማድረግ አንችልም። ምንም ጥቅም በሌላቸው እና ጊዜያዊ በሆኑ በሰዎች እና በቁሳቁሶች ላይ እምነታችንን እና ተስፋችንን ማድረግ ቅጣት አለው። ጥቅም እና በረከትን የምናገኘው እምነታችንን እና ተስፋችንን በእግዚአብሄር ላይ ስናደርግ ነው። የእግዚአብሄር ፀጋና ፍቅር ከሁሉም ነገር ይበልጣል።
4. በኢያሱ2፡9 መሰረት በእግዚአብሄር ፀጋ ላይ እንድንታመን የሚያደርጉ ነገሮች ምንድናቸው?

   ሀ.________________________________________

   ለ.________________________________________

   ሐ.________________________________________

   የምስጋናን መዝሙር መዘመር፤ የውዳሴን እና የአምልኮን መስዋዕት ማቅረብ በታማኝነት እግዚአብሄር ያደረገልንን መመስከር ይጠበቅብናል፤ "ማዳን የእግዚአብሄር ነው!"
5. ዮናስ ከአሳው ሆድ ውስጥ ከወጣ በኋላ ንስሃ በመግባት በአሳው ሆድ ውስጥ የነበረውን ሁኔታ ገልፆታል። በቁጥር 10 ላይ ምን ብሎ ነው የተናገረው?

____________________________________________

____________________________________________

**የቤት ስራ**፡ ትንቢተ ዮናስ ምዕራፍ 3 አንብቡት

**መልመጃ**

ዮናስ በአሳ ነባሪው ሆድ ውስጥ ለሶስት ቀናት ከቆየ በኋላ በባህሩ ዳርቻ ላይ የእርሱ ሁኔታ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት ይከብዳል፡፡ ደስተኛ ወይንም ሀዘንተኛ ወይንም ግራ የተጋባ ወይንም የተገረመ ሰው ሊሆን ይችላል፡፡ የእርሱ ሁኔታ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት ትችላላችሁ?

1. በቁጥር 1 ላይ ምን ሆነ?

___

2. በቁጥር 2 ላይ የተገለፀው ለዮናስ የመጣው የእግዚአብሄር ቃል ዋና ሃሳብ ምን ነበር?

___

___

3. ሃሰቡ እግዚአብሄር ለዮናስ በምዕራፍ 1፡2 ላይ ከተናገረው የተለየ ነበር?

___

እንደ ቁጥር 3 መሰረት የዮናስ ምልሽ ምን ነበር? በምዕራፍ 1፡3 ከተገለፀው አንፃር ምላሹ ምን ይመስል ነበር?

___

___

ከቁጥር 3-5 በተጠቀሰው መሰረት እግዚአብሄር ዮናስን እንዴት ተጠቀመበት?

___

___

4. የእግዚአብሄር መልዕክት ለነነዌ ሰዎች ደርሷል፡፡ መልዕክቱ ለንጉሱም ደረሰው (ቁጥር 6)፡፡ ንስሃ መግባታቸውን የሚያሳይ ነገር ንጉሱ ምን አደረገ?

   ሀ.___

   ለ. ___

   ሐ. ___

5. ከዚያም ንጉሱ አዋጅን አወጀ፡፡ የነነዌ ሰዎችን ወደ ንስሃ እና ፀሎት መራቸው፡፡ ንስሃው ማቅ መልበስን ያጠቃልል ነበር፤ ይህም በኃጢአታቸው እና ክፉ ስራቸው ማዘናቸውን፤ መፀፀታቸውን እና ትሁት መሆናቸውን የሚያመለክት ነው፡፡ ንስሃ የኃጢአት ልምምድን

ማቆምን፤ የክፋት አቅጣጫ መንገድን መቀየርን ያጠቃልላል። የነነዌ ሰዎች ለአደረጉት ነገር የእግዚአብሄር ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 10)?

---

የእግዚአብሄር በፀጋው የነነዌ ሰዎችን ንስሃ ተቀበለ፤ ሊደርስባቸውም ከነበረው ጥፋት አዳናቸው።

**ማሰላሰል**

ይህ አጭር ምዕራፍ በእግዚአብሄር ፀጋ የተሞላ ነው።

1. እግዚአብሄር ለዮናስ ዳግመኛ እድልን በመስጠት ምህረቱን አሳየው። ምንም እንኳን ዮናስ በእርሱ ላይ በማመፅ ባለመታዘዝ ተደብቆ ከእርሱ ቢሸሽም እግዚአብሄር ግን ለአላማው ሲል ዮናስን አዳነው፤ ቃሉንም ደግሞ እንዲህ ሲል ላከለት "________________________________________________________________________________________________________________________________________________::"
2. ዮናስ በመታዘዝ የእግዚአብሄርን ቃል ለማወጅ ሄደ፤ "________ ቀናት ውስጥ ነነዌ ____________________!"
3. ወሬውም ወደ ነነዌ ንጉሥ ደረሰ እርሱም ከዙፋኑ ተነሥቶ ____________________ ማቅም ለበሰ፥ ____________________ ። አዋጅም አስነገረ፥ በነነዌም ውስጥ የንጉሡንና የመኳንንቱን ትእዛዝ አሳወጀ፥እንዲህም አለ፦ ሰዎችና ________________________________________አይቅመሱ________________አይጠጡ።
4. በእግዚአብሄር ፀጋ፤ በእርሱ ገደብ የለሽ ፍቅር፤ ሰዎችና እንስሶችም በማቅ ይከደኑ፥ ወደ እግዚአብሔርም____________________ ሰዎችም ሁሉ ____________________በእጃቸው ካለው ____________________።
5. እግዚአብሔርም ከክፉ መንገዳቸው እንደተመለሱ ሥራቸውን አየ እግዚአብሔርም ________________________________________አላደረገውም።

**የማሰላሰል ጥያቄ**

1. እራሴን እንደዮናስ ወይንም እንደ ነነዌ ሰዎች አድርጌ ስመለከት ስለእግዚአብሄር ፀጋ ምን እማራለሁ? ______________________________________________________________________________________________________________________________________

2. እኛ አመፀኖች፤ የማንታዘዝ እና ደንዳና ልብ ያለን ሰዎች ስንሆን እንዲሁም ምርጫችን እና ተስፋችን በሌሎች ነገሮች ላይ ሆኖ እያለ እግዚአብሄር ለእኛ የነበረው የምስራች ምን ነበር? ______________________________

______________________________

3. እግዚአብሄር ስበድለው ዳግመኛ እድልን የሚሰጥ ይመስለኝ ነበር? ዳግመኛ እድልን እንዲሰጠኝ ጠይቄው አውቃለሁ?

______________________________

**ትግበራ**

ይህ ታሪክ በህይወቴ ላይ የሚያመጣው ለውጥ ምንድነው ብለን እስከምንጠይቅ ድረስ ጥናታችንን እቀጥላልን። ይህንን ፀጋ እንዴት አድርጌ ነው ልጠቀምበት የምችለው? ይህንን ፀጋ እንዴት አድርጌ ነው ለሌሎች እንዲደርስ የማደርገው? ምክንያቱም ፀጋ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሁሉንም ሰው እኩል ይወድዳል።

1. ለህይወቴ የእግዚአብሄር ፀጋ ለየት ባለመልኩ ያስፈለገኝ ወቅቱ መቼ ነው? ሌሎችን ሰዎች ለመውደድ፤ እራሴን ይቅር ለማለት እንዲሁም ሌሎችን ከመኮነን ለማቆም ይህ ፀጋ ያስፈለገኝ ወቅት አለ?

______________________________

2. በሌሎች እና በራሴ ላይ ስለፈፀምኩት በደል እራሴን ይቅር ማለት ያስፈልገኝ ይሆንን?

______________________________

______________________________

3. እግዚአብሄር ይቅር እንዳላችሁ እራሳችሁን ይቅር ማለት እንድትችሉ ፀጋውን ያብዛላችሁ።

4. ልወድዳቸው እየፈለግኩኝ ነገር ግን መውደድ ያልቻልኳቸው ሰዎች አሉ?

______________________________

5. እኔ ግን በራሴ ጥፋት ሌሎችንን ተጠያቂ ለማድረግ ብዙ ጊዜ ሞክሬያለሁ። ማድረግ የነበረብኝ ለሌሎች ምህረትን እና ርህራሄን ማድረግ ነበር። ከባድ ቢሆን እንዴት አድርጌ ነው በፀጋ ሌሎችን መውደድ የምችለው?

______________________________

______________________________

6. እግዚአብሄር ይቅር እንዳላችሁ ሌሎችን ይቅር ማለት እንድትችሉ እርሱ አቅምን ይስጣቸው፡፡

## ትምህርት 5

**የቤት ስራ**

ዮናስ 4 አንብቡት፡፡ ስለዮናስ ማንነት ወይንም ገፀ ባህሪይ በጥንቃቄ ተመልከቱ፡፡

**መግቢያ**

ይህንን ምዕራፍ ከአነበብን በኋላ ዮናስን ለመውደድ ሊከብደን ይችላል፡፡ እርሱ ግትር፤ የማይታዘዝ እና በራሱ ሃሳብ ብቻ የሚመራ ሰው ነው፡፡ እግዚአብሄር ወደ ነነዌ ሂድ ሲለው ለአለመታዘዝ ሲል በባህር ውስጥ መጣልን የመረጠ ሰው ነው፡፡ ይህ ምዕራፍ ዮናስ ለምን ወደ ነነዌ መሄድ እንዳልፈለገ ሀሳቦችን የምናገኝበት ነው፡፡ ጥናታችንን እንቀጥል…..

**መልመጃ**

1. በትንቢተ ዮናስ 3:10 ጌታ ለነነዌ ከተማ ነዋሪዎች እንዴት እንደራራላቸው እንመለከታለን፤ ለዚህ የጌታ ርህርሄ ዮናስ በምዕራፍ 4:1 ላይ የሰጠው ምላሽ ምን ነበር?

_______________________________________________________________

2. ዮናስ በቁጥር 2 ላይ ስለእግዚአብሄር ያወቀው እውነት ምንድነው 2?

   ሀ. ____________________________________________________

   ለ. ____________________________________________________

   ሐ. ____________________________________________________

   መ. ____________________________________________________

   ሠ. ____________________________________________________

3. እርሱ ስለሚያመልከው አምላክ የሚያውቀው እውነት ነበረው (ትንቢተ ዮናስ 1:9)፡፡ ለዚህም ነው መሸሽን የፈለገው፡፡ ይህ ተግባሩ ማለትም ወደነነዌ ከመሄድ መሸሹ ለነነዌ ሰዎች ስለነበረው አመለካከት ምን የሚነግረን ነገር አለው?

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

4. የነነዌ ሰዎችን እግዚአብሄር ምን እንዲያደርጋቸው ነው ዮናስ የፈለገው?

________________________________________________________

________________________________________________________

5. ጌታ እንዴት ነበር ምላሽን የሰጠው (ቁጥር 4)?

________________________________________________________

6. ዮናስ በነነዌ ላይ የሚሆነውን ለማየት ተዘጋጅቷል፡፡ የፀሃይ ሃሩር እንዳያቃጥለው እግዚአብሄር በፀጋው ጥላ እንዲሆነው የቅል ተክል እንዲበቅል አዘዘ፡፡ ስለዚህ ተክል ዮናስ የተሰማው ስሜት ምን ነበር (ቁጥር 6)?

________________________________________________________

7. እንደ ቁጥር 7 እና 8 መሰረት በነጋታው ምን ሆነ?

________________________________________________________

________________________________________________________

8. እንደገና ዮናስ ለመሞት ያለውን ፍላጎት ገለፀ፡፡ በነነዌ ሰዎች ላይ የተገለጠውን የእግዚአብሄርን ፀጋ በተመለከተ ጊዜ ቁጣውን መቆጣጠር አልቻለም፡፡ በደረቀችው የቅል ተክል ምክንያት እንደገና መሞትን መረጠ፡፡ በቁጥር 10 -11 ላይ ጌታ ለዮናስ ተግባር የሰጠው ምላሽ ምን ነበር?________________________________________

________________________________________________________

________________________________________________________

________________________________________________________

**አስተምሮ**

ዮናስ በነነዌ ከሚኖሩ ማን እንደፈጠራቸው፤እንደሚያፈቅራቸው እና ሊባርካቸው እንደሚፈልግ ከማያውቁ 120,000 ሰዎች ይልቅ ያስጨነቀው ስለደረቀችው የቅል ተክል ነበር፡፡ እነርሱ እግዚአብሄር ፀጋን እንደሚሰጥ፤ የሚራራ ፤ የፍቅር እና የምህረት አምላክ እንደሆነ አያውቁም ነበር፡፡ እንደ ዮናስ አመለካከት እርሱ እግዚአብሄርን መታዘዝ ያለበት የእስራኤል አምላክ ስለሆነ ብቻ ነው፡፡ እግዚአብሄር ግን ፀጋውን የእግዚአብሄር ህዝብ ተብለው ለማይታወቁ ለነነዌ ሰዎች ሊሰጥ ፈልጓል፡፡ ይህንንም በማድረግ እግዚአብሄር የሰዎች ሁሉ አምላክ መሆኑን አሳይቷል፡፡

**ማሰላሰል**

ይህ ታሪክ የሚያበቃው ጥያቄዎቻችንን ሳይመልስ ነው። እግዚአብሄር ለአቀረበው ታላቅ ጥያቄ ዮናስ እንዴት ነበር ምላሽን የሰጠው? እግዚአብሄር ከተገናኘው በኋላ ዮናስ ምን ሆነ? እግዚአብሄር በዮናስ ተግባር ትዕግስቱ አልቆ ገደለው? ይሁን እንጂ እነዚህ አስፈላጊ ጥያቄዎች ናቸው? ይህንን ታሪክ ወደ ዘመናችን እና ህይወታችን ስንተገብራቸው ሌሎች ተጨማሪ አስፈላጊ የሆኑ ጥያቄዎች ሊኖሩን ይችላሉ?

1. ከእኔ አመለካከት እና ከእኔ ብሔረሰብ የሚለዩ ሰዎችን እንዴት ነው የምመለከታቸው?
2. ሌሎች አማልክትን የሚያመልኩትን እንዴት ነው የምቆጥራቸው?
3. የጌታን ቃል እንዳካፍል በአካባቢዬ የሚኖሩ ሰዎች ሲጠይቁኝ የምሰጠው ምላሽ እንዴት ነው?
4. እርሱን ለማያውቁ ሰዎች የምሰጠው ምላሽ የእግዚአብሄርን ፍቅርን ምህረት የሚያሳይ ነው?

**ትግበራ**

የእርሱን ባህሪይ ለአለም እንድናንፀባርቅ እግዚአብሄር ጠርቶናል (ዘፍጥረት 1:27)። በዚህ ታሪክ ውስጥ ስለእግዚአብሄር ፀጋ ፣ ርህርሄ፣ ምህረት፣ ፍቅር እና ለቁጣ የዘገየ ባህሪውን እንማራለን። እርሱ በምንም መልኩ አድልኦን በሰዎች መካከል አያደርግም። ዮናስን በፍቅር እና በርህራሄ እንደተንከባከበ የነነዌ ሰዎችንም እንዲሁ ያለ ምንም ልዩነት ተንከንባክቧል። ማቴዎስ 5:43-48 አንብቡ። እየሱስ ወደ እርሱ ወደተሰበሰቡ ሰዎች ይህንን አስተማራቸው። ይህ ክፍል ለሌሎች ሰዎች ያለን አመለካከት የጌታን ማንነት የሚገልፅ በሚገልፅ መልኩ መሆን እንዳለበት ግድ ይለናል። እርሱ በመጀመሪያ የሚናገረው ስለ ፍቅር እና ጥላቻ ነው። ከዚያም ስለኃጢአት፣ እግዚአብሄር ዝናብን በኃጢአተኛ እና በፃዲቁ፣ በመልካም እና በክፉ ሰዎች ላይ እንደሚያዘንብ ይናገራል። እየሱስ ሰዎች እርሱ እንደሚያደርገው እንዲሁ እንዲያደርጉ ይጣራል። የሰዎች ተግባር የእርሱን ማንነት እንዲያንፀባርቅ ይጠራቸዋል። እግዚአብሄር ፍጥረቱን በዝናብ እና በፀሃይ ሲባርክ እየመረጣቸው አይደለም። የእኛም መልካምነት እንዲሁ እንዲሆን ግድ ይለናል። ሰውን እየመረጣችሁ አትውደዱ፣ ይልቁንም የሚጠሏችሁን ውደዱ። በልጁ በእየሱስ ክርስቶስ የቀደሰንን የእግዚአብሄርን ቅድስና እንድናንፀባርቅ ተጠርተናል። እኛ ፍፁማን መሆን ስለማንችል አዳኝ አስፈልጎናል!

**ማስታወስ**

በሚቀጥሉት ቀናት ውስጥ ማቴዎስ 5:44-45 እና 48 አስታውሷቸው። በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ እርሱ እንደወደዳችሁ ሌሎችን መውደድ እንድትችሉ ጌታ እንዲረዳችሁ ፃፉ።

**የማጠቃለያ አስተያየቶች**

ይህንን ጥናት ወደማጠቃለሉ ስንመጣ ትንቢተ ዮናስን አንድ ጊዜ እንድታነቡት ትበረታታላችሁ። በዚህን ወቅት "ግን" የሚለው ቃል ላይ ምልክት አድርጉበት።

1. ግን የሚለውን ቃላት ስትመለከቱ ለበርካታ ጊዜያት ተጠቅሰው ታገኛላችሁ።

   ሀ. ምዕራፍ አንድ ላይ ጌታ የሚናገረው ሌላ "ዮናስ ግን..." (ዮናስ 1:3)

   ለ. መርከበኞቹም ፈሩ፥ እያንዳንዱም ወደ አምላኩ ጮሁ፤ መርከቢቱም እንድትቀልላቸው በውስጥዋ የነበረውን ዕቃ ወደ ባሕር ጣሉት ዮናስ ግን ... (ዮናስ 1:5)።

   ሐ. ሰዎቹ ግን ወደ ምድሩ ሊመለሱ አጥብቀው ቀዘፉ ዳሩ ግን ...(ዮናስ 1:13)።

   መ. እግዚአብሄር ግን ....(ዮናስ 1:17

   ሠ. እኔም ከዓይንህ ፊት ተጣልሁ ነገር ግን...(ዮናስ 2: 5)።

   ረ. ወደ ተራሮች መሠረት ወረድሁ በምድርና በመወርወሪያዎችዋ ለዘላለም ተዘጋሁ አንተ ግን... (ዮናስ 2:7)።

2. ግን የሚለው ቃል በአብዛኛው በእግዚአብሄር እና በዮናስ መካከል ስለነበረው ክርክር የሚያሳይ ነው። ዮናስ ህይወቱን መምራት የሚፈልገው በራሱ መንገድ ነው። እግዚአብሄር ግን ሌላ ሃሳብ አለው። በምዕራፍ 3 ዮናስ እግዚአብሄርን ታዘዘ። እግዚአብሄር ዮናስ በነነዌ ከተማ የነበረውን አገልግሎት ባረከው። ህዝቡም አስፈላጊውን ምላሽ ሰጠ። በቁጥር 10 ላይ "እግዚአብሔርም ከክፉ መንገዳቸው እንደተመለሱ ሥራቸውን አየ ..." ከአለ በኋላ "ግን" አይልም። በዚህ ስፍራ በእግዚአብሄር እና በዮናስ፤ በሰው እና በተፈጥሮ፤ በቅል ተክል እና በትል መካከል ትግል የለም። ዮናስ ነነዌ ደረሰ፤ ህዝቡ ቃሉን ሰምተው ታዘዙ ... ወዘተ እያለ ቢተርክልን ኖሮ "ግን" የሚለውን ቃል አናገኝም ነበር።

**ፀሎት**

ሁሉን ቻይ የሆንክ ጌታ እግዚአብሔር እኔ እራሴን እንደ ዮናስ ሆኔ አገኘዋለሁ። እኔን ስትጠራኝ እኔ ደግሞ በሌላ አቅጣጫ ከፈቃድህ ውጭ እሄዳለሁ።ከአንተም ለመደበቅ

እሞክራለሁ፡፡ አንተን ለመታዘዝ ብዙ ጊዜ አልፈልግም፡፡ አንተን በአለመታዘዝ እና በአመፀኝነት የበደልኩትን ኃጢአቴን እናዘዛለሁ፡፡ ብዙ ጊዜ የራሴን መንገድ ነው የምመርጠው፡፡ እኔ ግትር ሰው ነኝ፡፡ የአንተን ርህራሄ ተጠቃሚ ለመሆን የተገባሁ ሰው አይደለሁም፡፡ ምንም እንኳን ኃጢአተኛ ብሆንም አንተ በፍቅርህ ወደ እኔ መምጣትህን አላቆምክም፡፡ አንተ የምታየውን ማየት እንድችል አይኖቼን ክፈትልኝ፡፡ ሌሎችን በማገልገል የአንተን ፍቅር ለሌሎች ማሳየት እንድችል ስለሰጠኸኝ እድል አመሰግንሃለሁ፡፡

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

# ክፍል ሁለት

# የልዑል አምላክ አገልጋዮች

# ትንቢተ ዳንኤል 1-6 — የዳንኤል ታሪክ

# ሲድራቅ፤ሚሳቅ እና አብድናጎ

---

## የክፍል ሁለት ቅኝት

### ቅኝት

*መግቢያ*

ክፍል 2፤ ዳንኤል 1-6

- *የንጉሱ ትዕዛዝ*
- *የእነዚህ ሰዎች ባህሪያት*
- *የንጉሱ አዋጅ*
- *ለመታዘዝ መበረታት*
- *ሶስት ሳይሆኑ አራት*
- *ቅኝት*

## መግቢያ

የንጉሱን ምግብ አንበላም ያሉት፣ ህልምን የተረጎሙት እና የሚያመልኩት አምላክ እግዚአብሄር ከሚነድደው እቶን እሳት ያድነናል ብለው ያመኑት እነዚህ ሰዎች እነማን ናቸው? የንጉሱን ትዕዛዝ በአለመታዘዝ እና እግዚአብሄርን በመታዘዝ ለመሞት ቆርጠው እንዲነሱ ያደረጋቸው ነገር ምድነው? እነዚህ ሰዎች የንጉሱን ቁጣ በአለመፍራት ፀንተው ቆሙ።

እነዚህን ሰዎች ለዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ያበቃቸው ነገር ምንድነው? ለአመኑት ጌታ ፀንተው እንዲቆሙ ያደረጋቸው ነገርስ ምንድነው? በእነርሱ ስለሚሰራው የእግዚአብሄር ሃይል የሰጡት ምስክርነት ውጤቱ ምንድነው? ስለ ሲድራቅ፣ሚሳቅ እና አብድናጎ ታሪክ ስታጠኑ የዚህን አይነት አስቸጋሪ ሁኔታ ቢገጥማችሁ ምን ታደርጋላችሁ፣ ማንንስ ታገለግላላችሁ? በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ከእኛ ጋር ሊሆን እግዚአብሄር ቃል ገብቷል። ሮሜ 8:28 "እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።" በማለት ተስፋን እና መፅናናትን ይሰጠናል። በማቴዎስ 28:20 ላይ ደግሞ እየሱስ ክርስቶስ እስከ አለም ፍፃሜ ድረስ ከእኛ ጋር እንደሚሆን ቃል ገብቶልናል።

## ትምህርት 2

**ክፍል 1**

***መግቢያ***

ዮናስ ትንቢት የተናረው በሰሜናዊው መንግስት በእስራኤል ነገስታት ዘመን ነበር (2 ነገስት 14:25)። በ2 ነገስት17:6 ላይ አሶራውያ እስራኤልንን ወርረው ዋና ከተማዋን ሰማርያን ይዘው ነበር። ከዚያም የእግዚአብሄር ህዝብ ተማርኮ ወደ አሶር ምድር ተጓጓዙ።

በ2 ነገስት 25 የምናነበው የይሁዳ ዋና ከተማ የሆነችው እየሩሳሌም በጠላት እጅ ሲትወድቅ እንመለከታለን። የባቢሎን ንጉስ የሆነው ንጉስ ናቡከደነፆር ወደ እየሩሳሌም ጦሩን አዝምቶ እየሩሳሌምን እና ቤተ መቅደሱን አቃጠለ፤ ህዝቡንም ማርኮ ወደ ባቢሎን ወሰዳቸው። አሁን ደግሞ በትምህርት ሁለት ውስጥ ከእነዚህ ምርኮኞች ውስጥ አንዱ ስለነበረው እና ኑሮውን በባቢሎን ስለአረገው ዳንኤል እንመለከታለን።

**የቤት ስራ**፤ ዳንኤል 1:1-21 አንብቡ

***መልመጃ***

1. በዳንኤል 1:1-2 የተመዘገበው ታሪክ ምንድነው?

   ሀ. የይሁዳ ንጉስ የነበረው ማን ነው?

   ______________________________________________

   ለ. የባቢሎን ንጉስ የነበረው ማን ነው?

   ______________________________________________

   ሐ. እግዚአብሄር ምን አደረገ?

   ______________________________________________

   ሐ. ህዝቡ ተማርከው ሄዱ። ሌላስ ተማርኮ የተወሰደ ነገር አለ?

   ______________________________________________

   መ. እነዚህ እቃዎች የት ነው የተቀመጡት?

   ______________________________________________

2.ንጉስ ናቡከደነፆር ለአስፋኔዝ ምን እንድያደርግ ነው ያዘዘው (ዳንኤል 1:3-5)?

ሀ. አልፋኔዝ የታዘዘው እነማንን እንዲከታተል ነው?

______________________________________________

ለ. የእነዚህ ወጣቶች ባህሪያትን ግለፁ?

i. ______________________________________________

ii. ______________________________________________

iii. ______________________________________________

iv. ______________________________________________

v. ______________________________________________

vi. ______________________________________________

ሐ. አልፋኔዝ ምንድነው የሚያስተምራቸው?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

መ. ንጉሱ ምንን አዘጋጀ?

______________________________________________

______________________________________________

ሠ. ከሶስት አመታት ስልጠና በኋላ ምን ይሆናል?

______________________________________________

______________________________________________

2. ከይሁዳ የመጡት አራቱ ሰዎች እነማን ናቸው (ቁጥር 6-7)?

| **አዲስ ስሞች** | **የቀድሞ ስሞች** |
|---|---|
| 1. | |
| 2. | |
| 3. | |
| 4. | |

3. ዳንኤል ግን በንጉሱ ትዕዛዝ አልተስማማም (ቁጥር 8).

ሀ. ችግር

______________________________________________________________

ለ. ጥያቄ

______________________________________________________________

4. ስለዳንኤል ጉዳይ እግዚአብሄር ያደረገው ጣልቃ ገብነት ምንድነው (ቁጥር 9)?

______________________________________________________________________

____________________________________________________________________

5. የሃላፊዎች ችግር ምን ነበር (ቁጥር 10)?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

6. ዳንኤል ከባለስልጣኑ ጋር ያደረገው ድርድር ምንድነው (ቁጥር 11-14)?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

7. የፈተናው ውጤት ምን ነበር (ቁጥር 15-16)?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

8. ለእነዚህ አራት ወጣቶች እግዚአብሄር የሰጣቸው ነገር ምንድነው (ቁጥር 17)?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

9. እግዚአብሄር ለዳንኤል በተለይ ያደረገለት ነገር ምንድነው?

____________________________________________________________________

10. ሰዎቹ ወደ ንጉስ ናቡከደነፆር የሚቀርቡበት ጊዜ ደረሰ፡፡

11. ንጉሱ የወሰነው ነገር ምንድነው (ቁጥር19)?

____________________________________________________________________

____________________________________________________________________

ሀ. እነርሱን ከአናገራቸው በኂላ ስለእነርሱ ያወቀው ነገር ምንድነው (ቁጥር 20)?

____________________________________________________

____________________________________________________

12. ዳንኤል ንጉሱን  ለምን ያህል ጊዜ አገለገለ?

____________________________________________________

**<u>ክፍል 2</u>:**

**ከህይወት ጋር ማዛመድ**

1. በእድሜአችሁ ወጣት ብትሆኑ እና የእነዚህን ወጣቶች፤ ማለትም የዳንኤልን እና የጓደኞቹን ታሪክ ብታነብቡ ምን አይነት ሃሳብ ወደ አዕምሮአችሁ ይመጣል?

____________________________________________________

____________________________________________________

____________________________________________________

2. የባህሪያቸው ዝርዝርን ስትሰሙ ምን ተሰማችሁ?

____________________________________________________

____________________________________________________

____________________________________________________

3. በቁጥር  9 ላይ እግዚአብሄር ባለስልጣናቱ ለዳንኤል መልካም ነገርን እንዲያደረጉለት አደረገ፡፡  በእናንተ በኩል እግዚአብሄር ለሌሎች ያደረገው መልካም ነገር ምንድነው?

____________________________________________________

____________________________________________________

4. ለእነዚህም ለአራቱ ብላቴኖች ____________________ በትምህርትና ____________________ ማስተዋልን ሰጣቸው ዳንኤልም ____________________ሁሉ ____________________ነበረ (ቁጥር 17)፡፡

5. እግዚአብሄር የሰጠህን/ሽ ስጦታዎች ምንድናቸው?

____________________________________________________

____________________________________________________

____________________________________________________

**ማስታወስ**

በዳንኤል 2 ላይ ናቡከደነፆር ህልም አለመ፤ ከዚያም የአገሩን ጠንቋዮችን አስጠርቶ የአለመውን ህልም እንዲነግሩት እና ህልሙን እንዲተረጉሙ ጠየቃቸው። ጠቋዮቹም ይህ የማይቻል ጉዳይ እንደሆነ ነገሩት። ህልሙን መተርጎም ይቻል እንደሆነ በማለት ዳንኤል ንጉሱን ጊዜ እንዲሰጠው ጠየቀ (ቁጥር 16)። ዳንኤል እና ሶስቱ ጓደኞቹ የህልሙን ትርጉም እንዲያውቁ እና በንጉሱ እንዳይገደሉ እግዚአብሄር እንዲረዳቸው ተማፀኑ። እግዚአብሄር ሚስጥሩን ለዳንኤል በራዕይ ገለጠለት። ከዚያም የእርሱ ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 20-23)? ______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

እነዚህን አራት ጥቅሶች በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ፃፉአቸው እና አጥኗቸው።

1. ጥበብ እና ስልጣን የማነው?

   ______________________________

2. ጥበብ እና እውቀትን የሚሰጠው ለማነው?

   ______________________________

3. ሚስጢርን እና በተሰወረ ቦታ የሚሆነውን ነገር የሚገልጥ ማነው?

   ______________________________

4. በቁጥር 23 ላይ ዳንኤል እውቅና የሰጠው ለማን ነው?

   ሀ.ጥበብንና ኃይልን ______________ ፥ እኛም የለመንንህን ነገር

   አሁን ____________::

   ለ. አንተ የአባቶቼ አምላክ ሆይ፥ የንጉሡን ነገር ______________፥

   ሐ. እገዛልሃለሁ ______________________::

**መግቢያ**

በትንቢተ ዳንኤል መፅሐፍ ውስጥ ቀጥለን የምናጠናው ምዕራፍ ሶስትን ነው። ማስታወስ የሚገባችሁ ነገር እነዚያ ሶስት ሰዎች በንጉሱ መንግስት ውስጥ አገልጋዮች መሆናቸውን

ነው። እነርሱ የሚኖሩት በባቢሎን እንግዶች እና ምርኮኞች ሆነው ነው። በዚህን ወቅት ነው ሶስቱ ሰዎች ለታላቅ ፈተና የተጋለጡት።

በምዕራፍ 2 መጨረሻ ላይ (ቁጥር 48-49) ዳንኤል ከፍተኛ ስልጣን እንዳገኘ እና በንጉስ ናቡከደነፆር ብዙ ስጦታዎችን እንደተሰጠው እንመለከታለን። በባቢሎን ግዛት ላይ እና በንጉሱ ጠቢባን ላይ ተሹሟል። በዳንኤል ጥያቄ መሰረት ሶስቱ ሰዎች፤ ሚሳቅ ፤ ስድራቅ እና አብድናጎ የአውራጃ ገዚዎች ሆነው ተሹመዋል። ዳንኤል ግን በቤተ መንግስት ውስጥ ተሹሞ ነው  እያገለገለ የሚገኘው።

**የቤት ስራ፤ ዳንኤል** 3:1-18 አንብቡት

***መልመጃ***

1. ንጉስ ናቡከደነፆር ስለአሰራው የወርቅ ምስል ምን እንማራለን (ቁጥር 1)?

______________________________________________

______________________________________________

2. ንጉሱ ምስሉን የሚመርቅበት ስነስርዓት ነበረው። በዚህ የምረቃ ስነስርዓት ላይ እነማን ናቸው የተጋበዙት (ቁጥር 2)?

______________________________________________

______________________________________________

3. ሲድራቅ፤ሚሳቅ እና አብዳናጎ እንደ አውራጃ ገዢነታቸው ተጋብዘዋል።
4. በቁጥር 4-5 ላይ የተጠቀሰው ትዕዛዝ ምን ነበር?

______________________________________________

______________________________________________

5. ትዕዛዙን አለመታዘዝ የሚያስከትለው ቅጣት ምንድነው (ቁጥር 6)?

______________________________________________

______________________________________________

6. ከዚያም ሙዚቃው ጀመረ፤ ቀጥሎም በዚያ የነበሩ ሰዎች ሁሉ ምን አደረጉ?

______________________________________________

7. የናቡከደነፆር ጠንቋዮች ምን የሚል ሪፖርት አቀረቡ (ቁጥር 8-12)?

______________________________________________

እነዚህ ጠንቋዮች የንጉሱን ህልም መተርጎም ባለመቻላቸው ምክንያት ግራ የተጋቡት ቢሆኑ ያደረጉት ነገር የሚያስገርም አይሆንም። እነዚህ ሰዎች ዳንኤል የንጉሱን ህልም በመተርጎሙ ምክንያት ከሞት የተረፉ ይሆንን?

8. ለሰማው ነገር ናቡከደነፆር የሰጠው ምላሽ ምንድነው (ቁጥር 13-15)?

ሀ. ሰዎቹ ተጠሩ

ለ. ሰዎቹ ተጠየቁ

ሐ. ሁለተኛ እድል ተሰጣቸው

9. የሲድራቅ፤ ሚሳቅ እና አብድናጎ ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 16-18)?

እነዚህ ሶስት ሰዎች ነገሮችን በግልፅ አስቀመጡ። የእነርሱ አምላክ ብቻ በግልፅ መመለክ የሚገባው እንደሆነ እና ከእርሱ በቀር ለማንም እንደማይሰግዱ ተናገሩ።

<u>**ክፍል 3**</u>

**ምልከታ**

የእነዚህ ሰዎች የእምነት ጥንካሬ የሚያስገርም ነገር ነው፤ ንጉሱ በሚቃጠለው የእቶን እሳት ሊገድላቸው እንደሚችል ቢያውቁም ከአቋማቸው ፍንክች አላሉም። አምላካቸው ሊያድናቸው እንደሚችል ያውቃሉ፤ ሊያድናቸው ፈቃዱ ባይሆንም እንኳን ለንጉሱ እርሱ ለአቆመው ምስል ወይንም ለሌላ ጣኦት እንደማይሰግዱ ገለፁለት (ቁጥር 18)።”

ይህንን ታሪክ የምናነብ አንዳንዶቻችን እግዚአብሄርን በማመናችን እና በማገልገላችን ምክንያት ለሞት የተጋለጥንበት ጊዜ ላይኖር ይችላል። አንዳንዶቻችን ግን ለስደት እና ለመከራ ተጋልጠን ይሆናል። ከእምነታችን የተነሳ በባለስልጣናት እና ሰዎች ፊት ቀርበን

ተጠይቀን፤ ታስረን ሊሆን ይችላል። በዚህ ዘመን በአገራችን መንግስታዊ ስደት የለም ነገር ግን ማህበራዊ መገለል፤ከቤተሰብ መባረር፤ ከስራ መባረር ... ወዘተ ሊገጥመን ይችላል። ይሁን እንጂ በዚህ ሁሉ መካከል እንደ ስድራቅ ፤ ሚሳቅ እና አብድናጎ እኛም አምላካችን ከገጠመን መከራ ሊያድነን ይችላል፡ ሊያድነን ባይፈቅድም እንኳን ከእርሱ በቀር ማንንም አናመልክም፤ ማንንም አናገለግልም ልንል ይገባል።

እነዚህ ሰዎች በንጉሱ አገር በባቢሎን አውራጃዎች ላይ ስልጣን እንዲያገኙ ያደረጋቸው ባህሪያቸው ወይንም ማንነታቸው አሁን ደግሞ ህይወታቸውን ለሞት ዳረገው። ንጉሱ ለአቆመው ምስል አልሰግድም ያሉበት ውሳኔአቸው ሊያስከትልባቸው የሚችለው ነገር በግልፅ ተነግሯቸዋል። የእነዚህ ሰዎች ውሳኔ እና ለአምላካቸው ያላቸው መሰጠት እንዴት የሚያስደንቅ ነው? እነዚህን ሰዎች ለዚህ ታላቅ ውሳኔ ያበቃቸው ነገር ምንድነው?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

ስለእነዚህ ሰዎች ያላችሁን አስተያየት ለሌሎች ሰዎች አካፍሉ:

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

**የቤት ስራ**: ዳንኤል 3:19-30 አንብቡት

**መልመጃ**:

1. ስድራቅ፤ሚሳቅ እና አብድናጎ ንጉሱ ለአቆመው ምስል ከሚሰግዱ ይልቅ መከራ መቀበል እና መሞትን እንደመረጡ ሲሰማ የናቡከደነፆር ሁኔታ ምን ሊመስል ይችላል?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

2. ናቡከደነፆር የአዘዘው ነገር ምንድነው (ቁጥር 19)?

________________________________________

3. የንጉሱ ትዕዛዝ ምንድነው (ቁጥር 20)?

______________________________________________________________

4.ስለሰዎቹ የተነገርን ነገር እነርሱ በጣም እንደደከማቸው እና ታስረው ወደ ሚነድደው እቶን እሳት እንደተጣሉ ነው፡፡ ከዚህ ምን ታስተውላላችሁ (ቁጥር 21)?

______________________________________________________________

ሀ. እነርሱን ወደ እሳቱ የጣሉአቸው ወታደሮች ምን ደረሰባቸው?

______________________________________________________________

ለ. የእግዚአብሄር ሰዎችስ ምን ሆኑ?

______________________________________________________________

5.የናቡከደነፆር ጥያቄ ምን ነበር (ቁጥር 24?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

ሀ. የተሰጠው መልስ ምንድነው?

______________________________________________________________

ለ. ናቡከደነፆር ምንን ተመለከተ? የአልተለመደው ነገርስ ምንድነው (ቁጥር25)?

i. ____________________________________________________

ii. ____________________________________________________

iii. ____________________________________________________

iv. ____________________________________________________

6.እነዚህ ሰዎች የንጉሱ አገልጋዮች ናቸው፡፡ ንጉሱ ምን አላቸው (ቁጥር 26) ?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

7. ከእቶን እሳት ውስጥ እንዲወጡ ንጉሱ ጠራቸው፡፡ ሰዎች ሁሉ ከበቧቸው፡፡ ሁሉም ሰዎች ስለሰዎቹ ያስተዋሉት ነገር ምንድነው?

ሀ.____________________________________________________

ለ. .___________________________________________________

ሐ.____________________________________________________

መ.____________________________________________________

8.ናቡከደነፆር ሶስቱን ሰዎች እንደራሱ አገልጋዮች ሳይሆን እንደ ልዑል አምላክ አገልጋዮች ነው የቆጠራቸው፡፡ ይህ ማለት (ቁጥር 28ለ) ለእርሱም ___________________አሳልፈው የሰጡትን ___________________የተላለፉትን በእርሱ የታመኑትን ___________________፥ የሲድራቅና የሚሳቅ የአብደናጎም ___________________፡፡

8.በቁጥር 29 ላይ የንጉሱ ትዕዛዝ ምን ነበር?

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

9. ለስድራቅ፤ ሚሳቅ እና አብድናጎ ንጉሱ ምን አደረገላቸው?

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

**<u>ክፍል 4</u>**

**ማገናዘብ**

የእነዚህ ወጣቶች ሃይለኛ ምስክርነት ለእኔ እና እናንተ ስለ እግዚአብሄር ታማኝነት ምን የሚያስተምረን ነገር አለው?

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

**ትግበራ**

1. በህይወቴ ውስጥ ያለው እቶን እሳት የሚያቃጥለኝ ላይሆን ይችላል፡፡ እሳቶቹ እምነቴን፤ ልምምዴን እና መታዘዜን የሚገዳደሩ ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እንዴት መኖር እችላለሁ? እምነቴ እና ለጌታ ያለኝን ምስክርነት ከሚፈታተኑ ነገሮች ሸሽቼ ልኑር? በህይወቴ መመስከር የሚገባኝ ለምን አይነት ነገሮች ነው?

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

2. ስለማመልከው እና ማገለግለው አምላክ ለመመስከር ምን አይነት ለውጥን በህይወቴ ማምጣት አለብኝ?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

**ፀሎት**

የማገለግልህ ሁሉን ቻይ የሆንክ ጌታ አምላክ ሆይ ለእኔ ያለህን ታማኝነት መመስከር በሚገባኝ ቦታ ሁሉ መስከር እንድችል አቅምን ስጠኝ፡፡ ሞትን የሚያስከትልብኝ ቢሆን እንኳን ሌሎች አማልክትን እንዳላመልክ እና የአንተን እውነተኛ አምላክነትን መመስከር እችል ዘንድ እርዳኝ፡፡ በዚያን ሁኔታ ውስጥ አንተ ሊታድነኝ ፈቃደኛ አለመሆንህን ባውቅም እንኳን ለአንተ ታማኝ እሆን ዘንድ አቅምን ስጠኝ፡፡ በዘመናት መካከል እጅግ በርካታ ለሆኑ ሰዎች መሰጠታቸው ታላቅ አርአያ ስለሆነው ስለእነዚህ ሶስት ወጣቶች አመሰግንሃለሁ፡፡  የእኔም ህይወት የአንተን ታማኝነት ለሌሎች የሚያሳይ እንዲሆን እርዳኝ፡፡

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

**ምልከታ**

በትንቢተ ዳንኤል 1:17 ላይ እንደምንመለከተው ዳንኤል ህልሞችን እና ራዕይን ያስተውል ነበር፡፡ በምዕራፍ ሁለት ደግሞ ንጉሱ ህልምን አልሞ የአገሩ ጥበበኞች ህልሙን እንዲነግሩት እና እንዲተረጉሙለት እንደጠየቃቸው እንመለከታለን፡፡ በምዕራፉ መጨረሻ ላይ ዳንኤል ህልሙን ተረጎመለት፡፡ ንጉሱም በዳንኤል ፊት በግንባሩ ተደፍቶ ከሰገደለት በኋላ የእህል ቁርባን እና እጣንም እንዲያርቡለት አዘዘ፡፡ ከዚህ ቀደም ብሎ እንደተገለፀው ንጉሱ ዳንኤልን በከፍተኛ ቦታ ከሾመው በኋላ በርካታ ስጦታዎችንም ሰጠው፡፡ በባቢሎን አውራጃ ላይም ሾመው፤ በአገሪቱ ጥበበኞችም ላይ አለቃ አደረገው፡፡

በምዕራፍ አራት ደግሞ በአገሩ የሚኖሩ ማናቸውም ጥበበኞች ሊተረጉሙት ያልቻሉትን ህልም አለመ። ንጉሱ እንደገና ወደ ዳንኤል መጥቶ የህልሙን ትርጉም እንዲነግረው ጠየቀው። በዚህን ጊዜ ዳንኤል ህልሙን ከተረጎመ በኋላ እንዲህ ብሎ ተናገረው፤ "ንጉሥ ሆይ፥ ስለዚህ ምናልባት የደኅንነትህ ዘመን ይረዝም እንደ ሆነ ምክሬ ደስ ያሰኝህ ኃጢአትህንም በጽድቅ፥ በደልህንም ለድሆች በመመጽወት አስቀር።" (ዳንኤል 4:27)

በምዕራፍ አምስት የንጉስ ናቡከድናፆር ልጅ ንጉስ ብልጣሶር ከሹማምንቱ ጋር የወይን ጠጅ እየጠጣ አባቱ ከእየሩሳሌም የእግዚአብሄር ቤተመቅደስ ያስመጣቸውን የወርቅ እና የብር ዋንጫዎች አስመጥቶ እየጠጣባቸው አማልክቱን ሲያመሰግን የሰው እጅ ጣጦች በግድግዳ ላይ ሲፅፉ ተመለከተ። የብልጣሶር ሚስት ስለዳንኤል ከነገረችው በኋላ ዳንኤልን አስጠራው። ዳንኤልም የተፃፈውን ፅሁፍ ሲያነበው የባቢሎን ታላቅነት እንደሚያበቃ አመላከተ። ብልጣሶር ዳንኤልን ሐምራዊ ልብስ እንዲያለብሱ እና ወርቅ ዘለበት በአንገቱ ላይ እንዲያደርጉ አዘዘ፤ በመንግስቱም ላይ ሶስተኛ ሰው አድርጎ ሾመው። ይሁን እንጂ በዚያው ምሽት ብልጣሶር ተገደለ፤የሜዶናዊው ዳርዮስ ስልጣኑን ወሰደው።

# ትምህርት ሶስት

# የህያው አምላክ አገልጋይ

# ዳንኤል 6 — ዳንኤል እና ንጉስ ዳርዮስ

---

**የትምህርት 3 ምልከታ**


ምልከታ

መግቢያ

ትምህርት 3፤ ዳንኤል 6

- ስህተትን ፍለጋ መሄድ
- የዳንኤል የፅድቅ ህይወት
- የዳንኤል የፀሎት ህይወት
- የንጉሱ አዋጅ
- በአንበሶች ዋሻ ውስጥ የነበረው ሌሊት
- አዲሱ አዋጅ

## መግቢያ

የሲድራቅ፤ የሚሳቅ እና የአብድናጎ እምነት ብቻ ሳይሆን የጓዳኞቻቸውም የዳንኤል እምነትም ተፈተነ፡፡ አሁንም እንደገና ክፉ ሰዎች የህያው አምላክ አገልጋይ የሆነውን የዳንኤልን ህይወት አደጋ ላይ ለመጣል እና እግዚአብሄርን ለመፈታተን ተነሱ፡፡ እነዚህን ሰዎች በክፋት እንዲነሳሱ ያደረገው ምንድነው? ዳንኤልን እንደዚህ እንዲያደርጉት ያደረጋቸው ነገር ምንድነው?

አንዴ የወጣ ህግ ወይንም አዋጅ ከተፈረመ በኋላ አይቀየርም፤ እነዚህም ሰዎች የንጉሱን ደካማ ጎን በመጠቀም እና ንጉሱ እንደአማልክት መመለክ እንደሚፈልግ ስለሚያውቁ ዳንኤልን የሚያጠቁበትን አዋጅ እንዲያወጣ በተንኮል ንጉሱን አግባቡት፡፡ ዳንኤል ሊታዘዘው የማይችለው እና በፍፁም የማይታዘዘው ንጉሱ ያወጣው አዋጅ ምንድነው? ችግሩ ምንድነው?

ዳንኤል ግን ጌታው አልካደም፡፡ እርሱ ንጉሱን በዚህ ጉዳይ አልታዘዘም፤ ቅጣቱም ደግሞ ሞት ነው፡፡ ስለዳንኤል ባህሪይ እና ህይወቱ ስታጠኑ ከእስራኤል አምላክ ጋር ያለውን ግንኙነትም አስተውሉ፡፡ እርሱ ስለእግዚአብሄር የሚያውቀው እውነት ምንድነው? ከእግዚአብሄር ጋር ያለውን ግንኙነት እንዲያሳድግ ያደረገው ምንድነው? ስርዓት ያለው የመንፈሳዊ ህይወት በረከት ምንድነው?

ዳንኤል ለንጉሱ ስለእግዚአብሄር ታማኝነት መሰከረ፡፡ ይህንንም በማድረግ ለንጉሱ ክፉ ምክርን የመከሩትን ሰዎችን ማንነት እና ክፉ አካሄድን አጋለጠ፡፡ ከአንበሶች ጋር በመኖር ዳንኤል የገለጠውን የእግዚአብሄርን ፀጋ በጥንቃቄ ተመልከቱ፡፡

## *መግቢያ*

**ክፍል1**

### *መግቢያ*

በትንቢተ ዳንኤል መፅሃፍ ውስጥ ህልሞች እና ራዕይዎች ተጠቅሰዋል፡፡ የእነዚህ ህልሞች እና ራዕይዎች ትንቢታዊ ትርጉም እና ፍፃሜአቸውም ተገልጧል፡፡ በዳንኤል 6 ውስጥ አንድ ታዋቂ እና አስገራሚ ታሪክን እናያለን፡፡ ያም ታሪክ ዳንኤል በአንበሳ ዋሻ ውስጥ ስለመጣሉ የሚናገር ነው፡፡ የባቢሎናውያን ስልጣን ዘመን አብቅቶ አሁን ደግሞ ምድሪቱን የሚገዙት ፋርሳውያን እና ሜዶናውያን ናቸው፡፡ ሜዶናዊው ንጉስ ዳርዮስ ዳንኤልን በደንብ አያውቀውም፡፡

**የቤት ስራ፤** ዳንኤል 6 አንብቡት

### *መልመጃ*

1.ንጉስ ዳርዮስ የዘረጋውን አስተዳደራዊ መዋቅር አጥኑት (ቁጥር 1-2)፡፡

ሀ. ______________________________________በመንግስቱ ላይ ተሾሙ፡፡

ለ. ሦስት ________________________ በላያቸው አደረገ ከእነርሱም አንደኛው ________________________ ነበረ፡፡

ሐ. የዳንኤል የስራ ድርሻ ምን ነበር (ቁጥር 3)?

_________________________________________________________________

መ. ከሌሎቹ ባለስልጣናት ዳንኤልን የሚለየው ምንድነው?

_________________________________________________________________

2. ይህ የስልጣን አወቃቀር ቅናትን አስከተለ፡፡ መሳፍንቱ እና አለቆች ምን ለማድረግ አሰቡ (ቁጥር 4)?

_________________________________________________________________

3. ዳንኤልን ለመክሰስ ምክንያት አላገኙም ነበር ምክንያቱም

_______________________________________________

4. ሰዎቹ ከመንግስት ሃላፊነቱ ጋር በተያያዘ ምንም ጥፋት አላገኙበትም። ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ነው ያስተዋሉት (ቁጥር 5)?

_______________________________________________

5. ለንጉሱ የአቀረቡት ሃሳብ ምን ነበር (ቁጥር 6-7)?

_______________________________________________

_______________________________________________

6.ንጉሱ ህጉን እንዳይቀይረው በማሰብ እነዚህ ሰዎች ንጉሱን ያሳሰቡት ነገር ምንድነው (ቁጥር 8)?

_______________________________________________

**ማሰላሰል**

ንጉሱ አዋጁን በፁሁፍ አደረገው። በፋርስ እና ሜዶን ህግ መሰረት አንድ አዋጅ አንድ ጊዜ ከወጣ ፈፅሞ አይሻርም።

1. እናንተ ንጉስ ብትሆኑ ህጉን እንድታወጡ እና እንድትፈርሙ የሚያደርጋችሁ ነገር ምድነው? የሰው ተፈጥሮ ፍላጎቱ ምንድነው?_______________________

_______________________________________________

2.ሰዎቹ ንጉሳቸውን እንዴት ነው የቀጠሩት? _______________________

_______________________________________________

3.ንጉሱ ይህንን ውሳኔ እንዲወስን ያደረገው ምንድነው?  ይህንን ተንኮል ያለበትን ሃሳብ እንዳያስተውል ያደረገው ነገር ምንድነው? _______________________

_______________________________________________

4.አስተዳዳሪዎቹ እና መሳፍንቱ በግልፅ ክፋት ያለበትን ሃሳብ ይዘው ወደ ንጉሱ መጡ። የዳንኤል ምን የተለየ ችሎታ ይመስላችኋል ሰዎቹን በቅንዓት እና በክፋት እንዲነሳሱ ያደረጋቸው (ዳንኤል 3)? _______________________

_______________________________________________

5.በምን በምን ባህሪያቸው እነዚህን ሰዎች ለይታችሁ ታውቃላችሁ? ንጉሱን? አስተዳዳሪዎችን እና መሳፍንቱን? ዳንኤልን? በእነዚህ ሰዎች ላይ ያላችሁን ሃሳብ እና ግንዛቤ አብራሩ:

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

**ትግበራ**

የዳንኤል ማንነት በፅድቅ ህይወቱ ተንፀባርቋል። ቁጥር 4 እንዲህ ይላል "የዚያን ጊዜም ____________ ስለ መንግሥቱ ____________ ነበር ነገር ግን ____________ ፥ ስሕተትና በደልም ____________ በእርሱ ላይ ____________ ዘንድ አልቻሉም።"

1.ዳንኤልን የመሰለ ሰራተኛን ለማሰራት የማይፈልግ አሰሪ ይኖር ይሆንን? እስኪ በተሰማራችሁበት የስራ ቦታ እና አገልግሎት ላይ ያላችሁን ታማኝነት ከዳንኤል ህይወት አንፃር ራሳችሁን ፈትሹ። ማንም ሰው እናንተን ተመልክቶ ከስራችሁ እና ባህሪያችሁ እንከንን ፈልጎ ያጣ ይሆንን?

______________________________________________

______________________________________________

2.የራሳችሁን የስራ ህይወት ስትፈትሹ የዳንኤልን የስራ ስነምግባር ታንፀባርቁ ይሆን?

________________________________________________

_______________________________________________

3.በየትኛው የህይወታችሁ እና የስራ አቅጣጫ ራሳችሁን ለመገምገም እና ለውጥ ለማድረግ ታስባላችሁ?

______________________________________________

______________________________________________

**ፀሎት**

4.ቃል ኪዳኑ ታድሷል። የእስራኤል ህዝብ ከግብፅ ባርነት ነፃ ወጥቶ የተስፋይቱን ምድር በወረሰ ጊዜ የተሰጣቸው የተስፋ ቃል አሁን ደግሞ የእነርሱ ነው፤ ከዚህም የተነሳ ቤተ

መቅደሱን መልሰው መገንባት ጀመሩ። በቁጥር 4ለ -5 ላይ የተገባላቸው የተስፋ ቃል ምንድነው?

________________________________________________________________

________________________________________________________________

_____________________________________________________________

**አስተምሮ**

በሐጌ 2፡7 ላይ ጌታ እንደገና ይህንን ቤት በክብሩ እንደሚሞላ ይናገራል! እርሱ አበክሮ የሚናገረው የዚህ የሁለተኛው ቤት ክብር ከመጀመሪያው ቤት እንደሚበልጥ ነው (ቁጥር 9)። እርሱ በዚህ ቤት ሰላምን እንደሚሰጥ ያረጋግጥላቸው (ቁጥር 9) እና ከዚህ ቀን ጀምሮ እንደሚባርካቸው ይናገራቸዋል (ቁጥር 19)።

**ክፍል 4**

***መልመጃ***:

1.በዚህን ጊዜ ትንቢትን የተናረው ሌላው ነቢይ ዘካሪያስ ነው። ትንቢተ ዘካሪያሰ ምዕራፍ አንድን ግለጡት። ህዝቡ ምን እንዲያደርግ ነው ነቢዩ ጥሪን የሚያቀርበው (ቁጥር 4)?

________________________________________________________________

________________________________________________________________

2.ቁጥር 6ለ ላይ "___________________________________________________

____________________________________________________________"አለ።

በእነዚህ የመጀመሪያ ምዕራፎች ላይ ስለ ንስሃ እንመለከታለን። ንስሃ ማለት ስለሰራነው የተሳሳተ ነገር ይቅርታን መጠየቅ አይደለም። ንስሃ ማለት ከክፉ ስራችን እና ልምምዳችን መመለስ ማለት ነው (ቁጥር 4)። ይህ ተግባር ወይንም ንስሃ መግባት ሙሉ በሙሉ ወይን 180 ድግሪ መመለስ ማለት ነው። ይህ ማለት በእግዚአብሄር ፊት ክፉ ለሆኑ ነገሮች ሁሉ ጀርባችንን መስጠት ማለት ነው።

3.እግዚአብሄር ለእየሩሳሌም ብልፅግናን እና ሰላምን ሊሰጥ ፈልጓል። እስራኤል የእርሱ እንደሆነች አውጇል። በትንቢተ ዘካሪያስ 2፡8-13 ላይ የሰማያዊው አባታችን ሃሳብ ምን እንደሆነ እናያለን።

ሀ.ቁጥር 8 ላይ ህዝቡን ምን በማለት ይገልፃቸዋል?

____________________________________________________________

ለ.እግዚአብሄር ህዝቡን ከርቀት ሆኖ የሚወድድ እና የሚያስተዳደር አምላክ ነው?

በቁጥር 10-11 ምንን እንማራለን?

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

_______________________________________________________________

አሁንም እንደገና እግዚአብሄር የእርሱ ከሆኑት ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዳላቸው እንመለከታለን፡፡ ህዝቡ እየሩሳሌምን መልሰው ለመገንባት ሲነሱ እርሱ ደግሞ ከእነርሱ ጋር ለመኖር ወሰነ፡፡

4.ወደ እየሩሳሌም በመመለስ ላይ የሚገኙት ሰዎች ደካሞች ፤አቅመ ቢስ እና ድሆች ነበሩ፡፡ ጉዞአቸው ረጅም እና አሰልቺ ነው፡፡ ነቢዩ ለዘሩባቤል የሚሰጠው ማፅናኛ ምን ነበር? የተሰጠውን ስራ ለመፈፀም ምን ያህል ጊዜን ይፈጃል (ዘካሪያስ 4:6)?

“በ_______________________________________________________________

________________________________________________________________::”

5.የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር ህዝቡ እርስ በእርሱ እንዴት እንዲሆን ነው የሚፈለግው (ዘካሪያስ 8:16-17)?

ሀ.______________________________________________________________

ለ.______________________________________________________________

ሐ.______________________________________________________________

መ.______________________________________________________________

ጌታ እግዚአብሄር እውነትን እና ሰላምን ይወድዳል፤ይህንን ስጦታ ለህዝቡ መስጠት ይፈልጋል፡፡

6.ትንቢተ ዘካሪያስ 13:9 የሚሰጠው ማበረታቻ ህዝቡ የእርሱ እንደሆኑ ነው፡፡ እግዚአብሄር ህዝቡን እንደ ብር እና እንደ ወርቅ እንደሚያጠራ ይናገራል፡፡ ከዚህን በኋላ እግዚአብሄር የገባው የተስፋ ቃል ምንድነው (ቁጥር 9ለ)?

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

**ማሰላሰል**:

ለምንድነው ትንቢተ ሐጌን እና ትንቢተ ዘካሪያስን የምናጠናው? እነዚህ ነቢያት የኖሩት ህዝቡ ከስደት ወደ እየሩሳሌም እየተመለሱ በነበሩበት ወቅት ነው፡፡ እነዚህ ነቢያት ከምርኮ ለተመለሰው በድካም እና በድህነት ውስጥ ላለው ህዝብ ከእግዚአብሄር የማፅናኛ እና የማበረታቻ መልዕክትን ያመጡ ነበር፡፡ በመሰረቱ ከምርኮ ተመላሾቹ ምንም ነገር የላቸውም፤ ነግ ግን እግዚአብሄር ቃል የገባላቸው እርሱ ከእነርሱ ጋር እንደሚሆን፤ አብሯቸው እንደሚኖር እና ስኬት የሚመጣው በመንፈሱ እንደሆነ ነው፡፡ የእነርሱ ከአገራቸው ውጭ በስደት የመኖር ኑሮ አበቃ፡፡ የእግዚአብሄር ቁጣ ወደ ርህራሄ ተለወጠ፡፡ እንደገና እርሱ በእየሩሳሌም ጉዳይ እንደሚቀና እና በታላቅ ትጋት ህዝቡን ከማንኛውም ጥቃት እንደሚጠብቅ ቃል ገባ፡፡

1. አሁን ደግሞ ወደ እዝራ 5 እንመለሳለን፡፡ ህዝቡን ነቢያቱ የማፅናኛ እና የማበረታቻ ቃላትን በሚናገሩበት ወቅት ዘሩባቤል እና ኢያሱ ደግሞ የእግዚአብሄር ቤትን ቤተ መቅደሱን መልሰው ይገነቡ ነበር፡፡ ምንም እንኳን ተቋውሞው የዘሩባቤልን እና የኢያሱን ስልጣን ቢገዳደረውም በእዝራ 5፡5 ላይ ምን እንደሆነ ተፅፏል?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

2.እግዚአብሄር ከእነርሱ ጋር እንደሚሆን የገባውን የተስፋ ቃሉን እና እርሱ ሁልጊዜ እንደሚጠብቃቸው በማመን ስራ መጀመራቸው ምን ዓይነት ስሜትን ይፈጥርባቸዋል? አስተያየታችሁን ስጡ:____________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

**መልመጃ**:

1.ዘሩባቤልን በብዙ ሁኔታ ከአስቸገረው በኋላ ተንትናይ ለንጉስ ዳርዮስ በእየሩሳሌም እየተከናወነ ስለሚገኘው ስራ ሪፖርት አቀረበ (እዝራ 5:6-17)፡፡ በምዕራፍ 6 ላይ ተንትናይ የንጉስ ዳርዮስን ምላሽን አገኘ፡፡ በባቢሎን በሚገኘው የመንግስት ግምጃ ቤት ወይንም መዝገብ ቤት ምንድነው የተገኘው (ቁጥር 3-5)?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

2.የንጉስ ዳርዮስ ትዕዛዝ እና አዋጅ ምን ነበር (ቁጥር 6-10)?

ሀ. ቁጥር 6-7:

____________________________________________________________

____________________________________________________________

ለ.ቁጥር 8-10:

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

3.በተጨማሪም እንደ ቁጥር 11-12 የንጉሱን ትዕዛዝ ባያከብሩ ወይንም ቢተላለፉት ወይንም ባይፈፅሙት የሚጠብቃቸው ነበር ምንድነው?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

**ማሰላሰል**:

የእግዚአብሄር መንፈስ በስራ ላይ መሆኑን እንመለከታለን። ንጉስ ዳርዮስ እንኳን ከእርሱ በፊት የነበረው ንጉስ ቂሮስ ምን እንዳዘዘ ለማወቅ መዝገብ ቤቱ እንዲፈተሽ አደረገ። ንጉስ ዳርዮስ የታወቁት ነገሮች ሁሉ በስርዓት እንዲሆን ስለፈለገ የሚያስፈልጉ ነገሮች ከንጉስ ካዝና እንዲሆን ትዕዛዝ ሰጠ። ዘሩባቤል፣ኢያሱ እና ህዝቡ እግዚአብሄር ከቁጥር በላይ በሆነ መንገድ እያበለፀጋቸው እና እየባረካቸው መሆኑን ተገነዘቡ።

1.አሁንም የምንመለከተው ነገር "የንጉሥ_______________ እንደ ውኃ ፈሳሾች _______________ እጅ ነው _______________ያዘነብለዋል (ምሳሌ 21:1)።"

2.የፋሲካ በዓል አከባበር እንዴት እንደነበር አሁን ደግሞ እንመለከታለን (እዝራ 6፡22)። እግዚአብሔር _______________፥ የእስራኤልንም አምላክ _______________ለመሥራት እጃቸውን ያጸና ዘንድ _______________ወደ እነርሱ መልሶአልና _______________ሰባት ቀን በደስታ አደረጉ።

3.ነገሮች የተረጋጉ ይመስላል። እዝራ 6:14 እንዲህ ይላል "_______________ ሽማግሌዎች በነቢዩ ______________________________ትንቢት ሠሩ ተከናወነላቸውም።"

ስለ ግንባታው ምክንያት ቁጥር 14ለ ምን ይላል? “እንደ ________________ ነገሥታት እንደ _________________እና እንደ _______________እና እንደ ________________ ትእዛዝ ሠርተው ፈጸሙ።

<u>ክፍል 5</u>

**መግቢያ**

ንጉስ አርጤክስስ ከንጉስ ዳርዮስ በመቀጠል የፋርስ መንግስት ንጉስ ሆነ። በንጉስ አርጤክስስ ዘመን እዝራ ከባቢሎን ወደ እየሩሳሌም መጣ። በመፃፊ እዝራ 7፡1-5 ላይ የእዝራ ትውልድ ሃረግ የተጠቀሰው ይህንን ይነግረናል። እርሱ ከካህናት ወገን ወይንም ጎሳ ነው።

**የቤት ስራ**: እዝራ 7 አንብቡት

ከእዝራ ጋር ከባቢሎን የመጣው ማነው?

ስለእዝራ ምን እንማራለን?

ንጉስ አርጤክስስ ለእዝራ የሰጠው ደብዳቤ ዋናው ሃሳብ ምንድነው?

መልመጃ:

1.ስለእዝራ ዝርዝር ሃሳቦችን እናገኛለን።

ሀ.በቁጥር 6 ላይ ስለእርሱ የተነገረን ምንድነው?

የእስራኤልም አምላክ እግዚአብሔር በሰጠው ______________________ነበረ የአምላኩም የእግዚአብሔር __________________________________ንጉሡ ____________ ሁሉ ሰጠው።

ሀ. በቁጥር 9 ላይ የተደገመው ቃል ምንድነው?

______________________________________________

ለ.በቁጥር 10 ላይ እዝራ በመስጠት ያደርግ የነበረው ምንድነው?

እዝራም _____________________________________ ፥ ለእስራኤልም _________________________________________ ዘንድ ልቡን አዘጋጅቶ ነበር።

2. ከእዝራ ጋር በመሆን ወደ እየሩሳሌም የመጡ ሰዎች እነማን ናቸው (ቁጥር 7)?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

3.ንጉስ አርጤክስስ ስለእዝራ የሚያውቀው እና እውቅና የሰጠው ነገር ምንድነው (ቁጥር 11-12)?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

4.ንጉስ አርጤክስስ ለእዝራ ደብዳቤን ፃፈለት (ቁጥር 12-26)። ከእዝራ ጋር ወደ እየሩሳሌም መሄድ የፈለጉ ሁሉ ተፈቀደላቸው። እዝራ ምን ማድረግ ነበረበት?

ሀ.ቁጥር 13-14:

______________________________________________________________________

_____________________________________________________________________

ለ.ቁጥር 15-16:

____________________________________________________________________

____________________________________________________________________

ሐ. ቁጥር 17:

______________________________________________________________________

_____________________________________________________________________

መ.ቁጥር 18-20:

___________________________________________________________________

___________________________________________________________________

___________________________________________________________________

5.ከወንዝ ማዶ ለነበረው አቃቤ ንዋይ (በጀሮንድ) የንጉሱ ትዕዛዝ ምን ነበር (ቁጥር 21-23)?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

6.በቁጥር 24 ላይ የንጉሱ ግልፅ ትዕዛዝ ምን ነበር (ቁጥር 24)?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

7.የንጉሱ ደብዳቤ የመጨረሻው ነጥብ ስለፍትሃዊ አስተዳደር ጉዳይ ነበር። በቁጥር 25 ላይ እዝራ በመጀመሪያ ዳኞችን እና ፈራጆችን _______________________።

ሀ. የእነርሱ ሃላፊነት ምንድነው?

________________________________________________

ለ.የእዝራ ስራ ምን ነበር?

________________________________________________

8.በቁጥር 26 መሰረት አለመታዘዝ የሚስከትለው ነገር ምንድነው?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

**ማሰላሰል**:

በንጉሱ ዘንድ እዝራ በስነ ምግባር የታነፀ ሰው እንደሆነ ታውቋል፡፡ ንጉሱ መንፈሳዊ ነገሮችን እንዲያከናውን ለእዝራ ውክልናን ሰጥቶታል፤በዚህም የእግዚአብሄር ህግ በስልጣን ላይ ባሉት ሰዎች ዘንድ ሁሉ በፍህታዊነት መተግበር አለበት፡፡ ይህንን ደግሞ በቁጥር 27-28 ላይ በግልፅ እንመለከታለን፡፡ እዝራ ይህንን ያደረገው የአባቶቻቸው አምላ እግዚአብሄር እንደሆነ አውቋል፡፡

1.ደግመን ምሳሌ 21፡ 1 እንመልከት "_______________እንደ ውኃ ፈሳሾች _______________ነው ወደ _______________፡፡"

2.በቁጥር 27-28 እውቅና የሚሰጠው ነገር ምንድነው?

ሀ. ንጉስን በተመለከት (ቁጥር 27):

_____________________________________________________________

ለ.እራሱን በተመለከተ (ቁጥር 28ሀ):

_____________________________________________________________

ሐ.እግዚአብሄርን በተመለከተ (ቁጥር 28ለ):

_____________________________________________________________

መ.እራሱን በተመለከተ (ቁጥር 28 ሐ)?

_____________________________________________________________

**የቤት ስራ**:

እዝራ 8:1-14 የቤተሰብ አባወራ ስም ዝርዝር እና አብሯቸው የተመዘገቡ የቤተሰብ ዝርዝርን የያዘ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ከባቢሎን ምድር ወደ እየሩሳሌም የተመለሱ ናቸው፡፡

እዝራ 8:15-23 አንብቡት

**መልመጃ**:

1. ወደ አኀዋም ወደሚፈስስ ወንዝ ሽለቆ እዝራ ሰበሰባቸው እና ማጣራት ጀመረ። በዚህን ጊዜ ምንን ነው ያረጋገጠው (ቁጥር15)?

_______________________________________________________________

2.አንድም ሌዋዊ ወደ እየሩሳሌም ለመመለስ ፈቃደኛ የሆነ የለም። ይህ ደግሞ የገጠመው ችግር ምንድነው (ቁጥር 17ለ)?

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

3.እዝራ የተወሰኑ መሪዎችን እና ሰዎችን በመሰብሰብ በካሲፍያ ወደሚገኘው መሪ ላካቸው። የእነዚህ ሰዎች ተልዕኮ ምን ነበር (ቁጥር 17)?

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

4.ተልዕኮው ተጠናቅቋል! ______________________ በብሩህ ሃሳብ የተሞላው ሌዋዊው ሰው ከልጆቹ እና ከቅርብ ዘመዶቹ ጋር ሆኖ መጣ። እነርሱም አብሯቸው ሌዋውያንን በስራ የሚያሿቸውን ሰዎች ይዘዋል (ቁጥር 18-20)። እነዚህ ሰዎች ለሰጡት ምላሽ የቀረበው ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 18)?

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

5. አንድ ሰው ቁጥር 21-23 ሲያነብ በመገረም ፈገግ ሊል ይችል ይሆናል። በመጀመሪያ እዝራ ያደረገው ነገር ___________________ያዋርዱ ዘንድ፥ ከእርሱም ___________________ለእነርሱ እና ለልጆቻቸውና ለንብረታቸውም ___________________ዘንድ በዚያ በአኀዋ ወንዝ አጠገብ ___________________። ከዚያም ቁጥር 22 እዝራ እራሱን ለጠላት ጥቃት አጋለጠ። እርሱ የአመነው ነገር ምንድነው?______________________________________________

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

6.ቀሪው ታሪክ ስለምን የሚናገር ነው (ቁጥር 31ለ)?

______________________________________________________________________

____________________________________________________________________

**ማሰላሰል**

እነዚህ ጥቅሶች ፈገግ አደረጓችሁ? በህይወታችሁ ውስጥ እምነትን የሚፈልግ ተግባር ገጥሟችሁ ያውቃል፤በእምነት የወሰዳችሁ እርምጃ አለ? እዝራ ንጉሱን ወታደሮች እና ፈረሰኞች እንዲሰጡት ለመጠየቅ አፈረ፡፡ እነዚህን ቢፈልግ እንደሚፈቀድለት ያውቃል፤ ይሁን እንጂ ለእርሱ ትልቁ ቁምነገር እርሱ እና አብረውት ያሉት ሰዎች ወደ እየሩሳሌም ሲመለሱ አምላካቸው እግዚአብሄር ከእርሱ እና ከህዝቡ ጋር መሆኑን ንጉሱ እንዲያውቅ ማድረጉ ነው (ቁጥር 18፡ 22)፡፡

እናንተ በእዝራ ቦታ ብትሆኑ፤የተሸናፊዎች ወይንም የምርኮኞች መሪ ሆናችሁ ከምርኮ ምድር ወደ አገራችሁ ስትመለሱ እርሱ የወሰደውን እርምጃ ትወስዱ ነበር? በዚህ ትምህርት ውስጥ እንደተመለከትነው እነዚህ ሰዎች ደካሞች፤ድሆች እና አቅመ ቢስ ሲሆኑ አራት ወራትን የሚፈጅ የእግር ጉዞ አደገኛ በሆነው ቦታ ሊያደርጉ ነው፡፡ በወታደሮች እና በፈረሰኞች መታመን ወይንስ አብሯቸው ሊሆን ቃል በገባው በማይታየው አምላክ መታመን? ይህ ቀላል ውሳኔ አይመስልም፤ቀላል ነገር ነውን? አስተያየታችሁን ፃፉት:

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

**የትግበራ ጥያቄዎች**:

1.በራሴ ህይወት ውስጥ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲገጥሙኝ በማን እና በምንድነው የምታመነው? በአለኝ ገንዘብ? በዘመዶቼ? በእውቀቴ? በስልጣኔ? በጓደኞቼ ወይንስ በምንድነው የምታመነው ወይንም እምነቴን የምጥለው በማን ላይ ነው?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

እግዚአብሄርን እርዳታ መጠየቅ ማለት በእርሱ ፊት እራሳችንን ማዋረድ ሲሆን ይህ ማለት ደግሞ እርሱ ካልረዳን እና ካልጠበቀን እኛ ምንም ማድረግ የማንችል አቅመ ቢስ እና ደካሞች ለአደጋ የተጋለጥን መሆናችንን እውቅና የምንሰጥበት ነው፡፡ ለዘላለሙ ተስፋዬን የምጥለው ወይንም ተስፋ የማደርገው ማንን ነው?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

***ፀሎት***:

*ሁሉን ቻይ የሆንክ ጌታ አምላክ ሆይ በፊትህ የምቀርበው በምስጋና እና በውዳሴ ፀሎት ብቻ ነው፡፡ እጆችህ ከእኔ ጋር ናቸው፡፡ እጅህ ለእኔ የማይገባኝ የፀጋ እና የፍቅር እጅ ነው፡፡ እኔ በአንተ እቅፍ ውስጥ ተመችቶኝ ነው የምኖረው፡፡ የአንተ ከእኔ ጋር መሆን ብርቱ የሚያደርገኝ ሲሆን አንተንም ቀሪ ዘመኔን እንዳገለግል ያስችለኛል፡፡ አንተ በመንፈስህ ብርቱ ስለአደረከኝ ምንም አልፈራም፡፡ በፀጋ በተሞላው እጅህ ስለባረከኝ አመሰግንሃለሁ፡፡ እኔም ለሌሎች መልካም እንዳደርግላቸው እርዳኝ፡፡*

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

***የመፅሐፈ እዝራ ማጠቃለያ***

*ምርኮኞቹ ከእዝራ ወደ እየሩሳሌም ተመልሰዋል፡፡ የተመረጡ ካህናት ብር፤ወርቅ እና በእግዚአብሄር ቤት ውስጥ እያገለገሉ ለሚገኙ ካህናት እና ሌዋውያ የተሰጠውን ስጦታ እንዲያመጡ ተለይተዋል፡፡ ለእግዚአብሄር መስዋዕቱ ከተሰዋ በኋላ ከንጉሱ ከወንዝ ማዶ ለሚገኘው ክልል አስተዳዳሪ የተላከው መልዕክት ተሰጠው (እዝራ 8:36)፡፡*

*መሪዎች ወደ እዝራ እየቀረቡ የእስራኤል ህዝብ ለአምላካቸው ለእግዚአብሄር ታማኝ እንዳልነበሩ ተናዘዙ፡፡ ምርኮኞቹም እራሳቸውን ወደ ምርኮ እንዲሄዱ ምክንያት ከሆነው ከጎረቤቶቻቸው እና ከእነርሱ ክፉ ተግባር አለዩም ነበር፡፡ ምርኮኞች ከሌሎች ሰዎች ጋር በጋብቻ ተጣመሩ፡፡ ይህ ተግባር እዝራን በጣም ነው ያበሻጨው ምክንያቱም ተግባራቸው*

በእግዚአብሄር የተከለከለ ስለሆነ ነው። በህዝቡ ኃጢአት እዝራ በእግዚአብሄር ፊት አፍሯል። እግዚአብሄር ግን በመልካምነቱ እና በፀጋው አዲስን ህይወት በመስጠት ቤተ መቅደሱን እና የእየሩሳሌምን ቅጥር እንደገና እንዲገነቡ አደረጋቸው። አሁንም ህዝቡ ለእርሱ ትዕዛዝ ብዙም ትኩረት አልሰጡም። ምድሪቱ በእግዚአብሄር ኃጢአት ተበክላለች።

እዝራ ወደ እግዚአብሄር፤ ወደ እስራኤል አምላክ ፤ ወደ ፃዲቁ ፀለየ። "አቤቱ የእስራኤል አምላክ ሆይ፥ አንተ ጻድቅ ነህ ዛሬም እንደ ሆነው እኛ አምልጠን ቀርተናል እነሆ በፊትህ በበደላችን አለን ስለዚህ በፊትህ ሊቆም የሚችል የለም (እዝራ 9:15) ።" እስራኤላውያን የውጭ አገር ሴቶችን በማግባታቸው ምክንያት በእግዚአብሄር ላይ ስለፈፀሙት ታማኝነትን የማጉደል ተግባር ንስሃ ገባ። በእዝራ 10:11 ካህኑ እዝራ ለህዝቡ ኃጢአታቸውን በማስታወቅ ንስሃ ገብተው የእግዚአብሄርን ፈቃድ እንዲፈፅሙ አሳሰባቸው። እርሱ ህዝቡ እራሳቸውን በዙሪያቸው ከሚኖሩ ህዝቦች እና ከባዕዳን ሚስቶቻቸው እንዲለዩ አዘዛቸው። እነርሱም አደረጉት (ቁጥር 16)።

# ትምህርት ስድስት

# አንተ ፃዲቅ ነህ

# ነህምያ 1-13 — የነህምያ ታሪክ

---

### የትምህርት 6 ምልከታ

ምልከታ

መግቢያ

ትምህርት 6: ነህምያ 1-13

- የነህምያ ፀሎት
- ከባድ ተቃውሞ
- የቅጥሩ ግንባታ ተጠናቀቀ
- ህዝቡ ራሳቸውን አቋቁመው መኖር ጀመሩ
- የዳስ በዓል
- ህጉን ማንበብ
- መናዘዝ እና ንስሃ መግባት
- የቅጥሩ ምረቃ

# መግቢያ

መፅሐፈ ነህምያ ምዕራፍ አንድ የሚጀምረው ሰዎች ወደ ነህምያ ሪፖርትን ይዘው መምጣታቸውን በመተረክ ነው፡፡ እነርሱም ከምርኮ ወደ ይሁዳ የተመለሰው ህዝብ ያለበትን ሁኔታ ለነህምያ ነገሩት፡፡ እነርሱ የነገሩት ነገር ስለረበሸው ነህምያ ጉዳዩን ይዞ ወደ እግዚአብሄር መፀለይ ጀመረ፡፡ እርሱም የንጉሱ የወይን ጠጅ አሳላፊ ስለነበር እርሱን የረበሸውን ነገር ንጉሱ እንዲሰማው እድል ሰጠው፡፡

ይህንን ትምህርት ስታጠኑ ነህምያ ወደ እየሩሳሌም ተመልሶ ምን እንደገጠመው በደንብ ተመልከቱ፡፡ ችግሩ ምን ነበር? በአስቸኳይ መደረግ የነበረበት ነገር ምንድነው? የተጀመረው ስራ እንዳይጠናቀቅ በስራ ላይ ያለውን ህዝብ ተስፋ የሚያስቆርጥ ታላቅ ተቃውሞ ተነሳ፡፡ የእየሩሳሌምን ቅጥር ግንባታ ለማስቆም ከፍተኛ ጥረት ቢደረግም የቅጥሩ ግንባታ ግን በድል ተጠናቀቀ፡፡

እዝራ የሙሴን የህግ መፅሐፍ በአነበበ ጊዜ ሁሉም ሰዎች ሰሙት፡፡ የሙሴን ህግ የማንበቡ ውጤት ምን ነበር? የህዝቡ ምላሽ ምን ነበር? ህዝቡ ግን ያደረገው “አንተ ብቻህን ጌታ ነህ” ብሎ ማወጅን ነበር፡፡ እነርሱም የእነርሱ መቤዤት የተመሰረተው ቁጣው በዘገየ እና ፍቅሩ በበዛ ፃዲቅ አምላክ ላይ መሆኑን አወቁ፡፡ አባቶቻቸው እና ከዚያ በፊት የነበረው ትውልድ በልበ ደንዳናነት ለፈፀሙት ተግባር ፃዲቁ እግዚአብሄር ያደረገው ሁሉ ተነገራቸው፡፡ አሁንም እግዚአብሄር በታማኝነቱ ለአባቶቻቸው ለአብረሃም፤ለይስሃቅ እና ለያይቆብ ሊሰጣቸው ቃል ወደ ገባላቸው ምድር መመለሳቸውን እና እዝራ እና ነህምያ ደግሞ የተረፉት ቅሬታ አካል በመሆን እግዚአብሄር በሰጣቸው ምድር ተመልሰው የመልሶ ግንባታን ስራ ሊያካሂዱ ነው፡፡

# ትምህርት 6

## ክፍል 1

**መግቢያ**:

በቢሉይ ኪዳን ከእዝራ መፅሐፍ ቀጥሎ የምናገኘው መፅሐፈ ነህምያን ነው። በመፅሐፈ ነህምያ ውስጥ የሚገኘው ታሪክ የተከናወነው ከአመታት በኂላ ነው። የመፅሐፉ የመጀመሪያ ሰባት ምዕራፎች ዋናው ትኩረት ስለእየሩሳሌም ቅጥር እና በሮች ግንባታ ነው። ቅጥሩ ሁሌ ከሚኖረው ጥቃት ከተማዋን ይጠብቃታል። የጠላቶቻቸው የከፋ ተቃውሞ ለሰራተኞቹ የግንባታውን ስራ አስቸጋሪ አድርጎል።

በመፅሐፈ ነህምያ 8 የእግዚአብሄር ህግ ተነበበ። በምዕራፍ 9 ህዝቡ ኃጢአታቸውን ከተናዘዙ በኂላ እንደ እግዚአብሄር ህግ ለመኖር ቃል ገቡ። ህዝቡም በእየሩሳሌም እና በይሁዳ ምድር ሁሉ ሰፍረው መኖር ጀመሩ። በምዕራፍ 12 ቅጥሩ ተጠናቅቆ ተመረቀ። በምዕራፍ 13 ተሃድሶ ተከናወነ። ያለጥርጥር በጥናታችን ውስጥ ብዙ ነገሮችን እናያለን፤ ይሁን እንጂ ሁሉንም በጥልቀት ለማየት ጊዜ ስለማይበቃን የተወሰኑትን ብቻ እንመለከታለን። አሁን ጥናታችንን እንቀጥል!

**የቤት ስራ**: ነህምያ 1 አንብቡ

**መልመጃ**:

1.ነህምያ ከይሁዳ ከመጡት ሰዎች የተቀበለው ሪፖርት ወይንም የሰማው ነገር ምንድነው (ቁጥር 1-3)?

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

2.ነህምያ የተነገረውን ከሰማ በኂላ ሁኔታው እንዴት ነበር (ቁጥር 4)?

________________________________________________

________________________________________________

3.የነህምያ ፀሎት ዋናው ሃሳብ ምንድነው?

ሀ.ቁጥር 5-6ሀ:

---

ለ.ቁጥር 6ለ-7:

---

መ.ቁጥር 8-9:

---

መ.ቁጥር 10-11:

---

በዚህ ፀሎት ውስጥ የምንመለከተው ነገር ነህምያ በመጀመሪያ ወደ እግዚአብሄር ፀለየ ቀጥሎም ለእስራኤል ህዝብ ፀለየ፡፡ ቀጣዩ የንስሐ ፀሎት የራሱን ጨምሮ የህዝቡን ለእግዚአብሄር ህግ አለመታዘዝ እየተናዘዘ ንስሃ እየገባ መፀለይ ነበር፡፡ ከዚህም በመቀጠል እግዚአብሄር ለህዝቡ የገባው የተስፋ ቃል እያሳሰበ ይፀልይ ነበር፡፡ የተስፋው ቃል አለመታዘዝ የሚያስከትለውን መዘዝ (ኦሪት ዘሌዋውያን 26:33) እና በመታዘዝ የሚመጣውን በረከት (ኦሪት ዘዳግም 30:4) ያጠቃለለ ነበር፡፡ የነህምያ የመጨረሻው ፀሎት እግዚአብሄር በንጉሱ ፊት ሞገስ እንዲሰጠው ነበር፡፡

የነህምያ ኃላፊነት ምን ነበር (የቁጥር 11 መጨረሻ)?

---

**ማሰላሰል**

የነህምያ ፀሎት ለእኛ ፀሎት ትልቅ ምሳሌ የሚሆን ነው፡፡ ወደ ማን እንደሚፀልይ እና የአምላኩን ታላቅነት ያውቃል፡፡ ለሌሎች ከፀለየ በኋላ እግዚአብሄር ለህዝቡ የገባውን የተስፋ ቃል እያስታወሰ ይፀልያል፡፡ ከዚህ በኋላ ነህምያ ለህዝቡ በተለይም በብዙ ጉስቁልና ውስጥ ለሚገኘው ህዝብ መፍትሄ መሆን እንዲችል ፀለየ፡፡

1.የራሳችሁን ፀሎት ምን እንደሚመስል እስኪ ጊዜ ወስዳችሁ አስቡት፡፡ የራሳችሁን ፀሎት ልታዳብሩበት ከምትችሉበት ከነህምያ ፀሎት ምን ተማራችሁ?

---

---

2.አዲስ አማኝ ወይንም ትንሽ ልጅ በግል ሆነ ሰዎች በተሰበሰቡበት ቦታ እንዴት መፀለይ እንዳለባቸው ቢጠይቋችሁ ምን አይነት ምክር ትሰጣላችሁ?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

**የቤት ስራ**: ነህምያ 2 አንብቡት.

**አስተምሮ**

ነህምያ ለንጉሱ የወይን ጠጅ አሳላፊ ነበር (ነህምያ 1:11)። የወይን ጠጅ አሳላፊው በንጉሱ የታመነ ሰው ሲሆን ለንጉሱም በምግብ ሰዓት የወይን ጠጅ ያቀርብለታል። የወይን ጠጅ አሳላፊው ለንጉሱ የወይን ጠጁን ከማቅረቡ በፊት መቅመስ አለበት፤ ይህ በሚሆንበት ወቅት ንጉሱን መርዞ ለመግደል በሌሎች ሰዎች የወይን ጠጁ ውስጥ መርዝ ተጨምሮ ከሆነ ቀድሞ የሚሞተው ነህሚያ ነው ማለት ነው። ነህምያ የንጉሱ የወይን ጠጅ አሳላፊ መሆኑ ህይወቱን ለከፍተኛ አደጋ አጋልጦት ነው። ነህምያ የንጉስ አርጤክስስ የተከበረ ሃላፊ ሆኖ አገልግሏል።

**መልመጃ**:

1.በቁጥር 1 እና 2 ላይ ንጉሱ ምንን ተመለከተ?

______________________________________________

2. የነህምያ ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 3)?

______________________________________________

3.ለንጉሱ ጥያቄ የሰጠው ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 4 እና 5)?

______________________________________________

______________________________________________

4.እርሱ በንጉሱ ፊት ሞገስን አገኘ፤ ወደ እየሩሳሌም በመሄድ መልሶ እንዲገነባ ፈቃድን ከንጉሱ አገኘ። ቀጥሎም ነህምያ ተጨማሪ ነገርን ጠየቀ። በቁጥር 7 እና 8 ላይ የጠየቀው ነገር ምንድነው?

______________________________________________

______________________________________________

5.እርሱ ከጠየቀው ነገር ከተጨማሪ ንጉሱ ምን ሰጠው (ቁጥር 9)?

________________________________________________________________

**ማሰላሰል**:

*የነህምያ በቁጥር 8 ላይ "...መልካም እንደሆነችው እንደ አምላኬ እጅ" በማለት በተናገረው ነገር ብዙም ልንደነቅ አይገባም፡፡ ይህ አባባል ግን የተለመደ ነገር ነው?*

***ማስታወሻ*** ፧

*የእዝራ መፅሐፍ መልካም ስለሆነው የእግዚአብሄር እጅ ወይንም በፀጋ ስለተሞላው የእግዚአብሄር እጅ ስድስት ጊዜ ይናገራል! እነዚህን ክፍሎች ክፈቱ እና ቃላቱ ላይ አስምሩበት፡፡ እዝራ 7:6, 9, 28; እና እዝራ 8:18, 22, 31 ተመልከቱ፡፡*

*አሁን ደግሞ ነህምያ ተመሳሳይ ቃላትን ይጠቀማል፡፡ "መልካም የሆነው የአምላኬ እጅ" የሚለው አባባል ለእናተ ምን ትርጉም ይሰጣል? መልካም የሆነውን የእግዚአብሄርን እጅ እንዴት በህይወታችሁ ተለማመዳችሁት?*______________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

**መልመጃ**:

1.የቤተ መቅደሱ ግንባታ መሰረት በተጣለ ጊዜ ተቃውሞ ተነስቶ እንደነበር በመፅሐፈ እዝራ ውስጥ ተመልክናል፡፡ አሁን ደግሞ ተቃውሞን የመሩት ሰዎች እነማን ናቸው (ነህምያ 2:10)?

ሀ.________________________________________________

ለ.________________________________________________

1.እነርሱን የረበሸው ነገር ምንድነው?

________________________________________________________________

________________________________________________________________

2.በቁጥር 11-16 ውስጥ እየሆነ ያለው ነገር ምንድነው ?

________________________________________________________________

3.በቁጥር 17-18 ውስጥ ነህምያ እቅዱን ገልጧል፡፡ በእግዚአብሄር መልካም እና በፀጋ የተሞላ እጅ እና በንጉሱ ድጋፍ ነህምያ ምን ሊሰራ አቀደ?

4.የእየሩሳሌም ቅጥር መልሶ በመገንባቱ ምክንያት የሚወገደው ነገር ምድነው?

______________________________________________________________________

5.የህዝቡስ ምላሽ ምን ነበር?

______________________________________________________________________

6.ቁጥር 19 ላይ የተጠቀሰው ችግር ምንድነው? የተቃዋሚዎች ክስ ምን ነበር?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

_____________________________________________________________________

7.ነህምያ ለተቃዋሚዎች የመለሰላቸው ነገሮችን በቀጥታ በመናገር ነበር፡፡ እንዴት ነበር የመለሰላቸው? ________________________________________________________

______________________________________________________________________

**የቤት ስራ**:

ምዕራፍ 3 የሚናገረን ቅጥሩን የሚገነቡ እነማን እንደነበሩ እና የሚገነቡበትን ቦታዎችን ነው፡፡ ምዕራፍ ሶስትን ገረፍ ገረፍ አድርጋችሁ ተመልከቱ እና "በአጠገባቸውም" የሚለውን ቃል አስምሩበት፡፡ ስራው የተሰራው አንዱ ከአንዱ አጠገብ በመገንባቱ ነው፡፡ ስራው የተሰራው የፈረሰውን እና የተቃጠለውን ቅጥር እና በሮችን መልሶ በመገንባት ነበር፡፡

ነህምያ 4 አንብቡት

**መልመጃ**:

1.ሰንበላጥ እና ጦቢያ አይሁዶች መቃወማቸውን ቀጠሉ፡፡ ሰንበላጥ በጣም ተናድዷል፤ ተበሳጭቷልም፡፡ እርሱ በስራው ላይ ያላገጠበት ምክንያት ምን ነበር (ቁጥር 1-2)?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

ጦቢያ የተናገረው ነገር ምንድነው (ቁጥር 3)?

______________________________________________________________________

2.የእግዚአብሄር ህዝብ ምላሽ የሚያስደስት ነው፡፡ ከተቃዋሚዎች ጋር አልተከራከሩም፡፡ ይልቁንም ወደ ጌታ አምላቸው ተመለሱ፡፡ ፀሎታቸውን አጠቃላችሁ ፃፉት (ቁጥር 4-5)?

______________________________________________________________________

3.ትኩረታቸውን ወደ ጌታ ከአደረጉ በኂላ ምን ሆነ (ቁጥር 6)?

ሀ.ስራውን በተመለከተ:

ለ.ህዝቡን በተመለከተ:

4.የእነርሱ ማላገጥ በስራው ላይ ምንም ለውጥ እንዳላመጣ በተገነዘቡ ጊዜ ተቃዋሚዎቹ ስራውን ለማስቆም ምን ለማድረግ አሰቡ?

5.እስራኤላውያን ለጠላቶቻቸው ተቃውሞ እና ዛቻ ምን አደረጉ (ቁጥር 9)?

6.በግንባታው ስራ ላይ በተሰማሩ ሰዎች ላይ ምን ደረሰባቸው (ቁጥር 10)?

7.የህዝቡ ሞራል ምን ሆነ (ቁጥር 11-12)?

8.ነህምያ ህዝቡን ሰይፍ፤ጦር እና ቀስትን አስታጥቆ የማበረታቻ ንግግር ተናገራቸው (ቁጥር 14):

9.እግዚአብሄር የጠላትን ስራ እያፈራረሰ የራሱ የሆኑትን የህዝቡን ስራ ደግሞ ይባርክ ነበር (ቁጥር 15).

10.ቀሪው የምዕራፉ ክፍል የሚናገረን የሰራተኞቹን የመከላከል ስልት ነበር። ሁሉም ሰራተኞች ስራውን ሲሰሩ የጦር መሳርያቸውን ይዘው ነበር ስራቸውን የሚሰሩት። ስራው ታላቅ እና ሰፊ ስለነበር (ቁጥር 19) የተነገራቸው ነገር መለከት ሲነፋ ሁሉም በአንድነት እንዲሰበሰቡ ነው፤ እግዚአብሄር ስለእነርሱ ይዋጋል እና (ቁጥር 20)። ለሰራተኞቹ የነህምያ መመሪያ ምን ነበር (ቁጥር 22)?

**አስተምሮ**:

ነህምያ 5 በህዝቡ ዘንድ ስለነበረው የገንዘብ ችግር ይናገራል፡፡ ከነበራቸው ችግር የተነሳ መሬት እና እርሻቸውን አስይዘው በመበደር እህል ይገዙ እና ለንጉሱም ግብር ይከፍሉ ነበር፡፡ ወንድ እና ሴት ልጆቻቸው ሳይቀሩ ለባርነት ተጋልጠው ነበር፡፡ ነህምያ ታላላቆቹን እና ሹማምንቱን ከወቀሳቸው በኋላ የወንድሞቻቸውን የእርሻ መሬት መልሰው እንዲሰጧቸው እና በወንድሞቻቸው መከራ እና ስቃይ አላስፈላጊ ሃብትን እንዳያካብቱ አሳሰባቸው፡፡ ታላላቆች እና ሹማምንቱ ነህምያ እንዳዘዛቸው ለማድረግ ቃል ገቡ፡፡ ነህምያም ለህዝቡ ምሳሌ ለመሆን ሲል እንደ አስተዳዳሪነቱ ከእርሱ በፊት የነበሩት እንደሚያደርጉት የተመደበለትን በጀት በሙሉ አይጠቀምም ነበር፡፡ ይልቁንም እርሱ እና የእርሱ ሰዎች በእየሩሳሌም ቅጥር መልሶ ግንባታ ላይ ይተጉ ነበር (ቁጥር 16)፡፡ በእርሱ ገበታ ላይ በየቀኑ 150 አይሁድ፤ባለስልጣናት እና በአካባቢያቸው ከሚኖሩ ህዝቦች የመጡ አብረውት ይመገቡ ነበር፡፡

**የቤት ስራ**: ነህምያ 6:1-14 አንብቡት

ነህምያን ለመጉዳት የተደረጉት ሙከራዎች ምን ነበሩ?

እያንዳንዱ ተቃውሞ የሚመጣው ከየት ነበር?

**መልመጃ**:

1.የነህምያ ጠላቶች ተስፋ ቆርጠው የሚያደርጉትን ተቃውሞ አላቆሙም፡፡ እነርሱ አድብተው እርሱን ለመጉዳት እንደፈለጉ እርሱ አውቋል፡፡ የእነርሱ ግብዣ ምን ነበር (ቁጥር 2)?

___________________________________________

2. የነህምያ ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 3-4)?

___________________________________________

___________________________________________

___________________________________________

3.በደብዳቤያቸው የጠቀሱት የመጀመሪያው ክስ ምን ነበር (ቁጥር 5-7)?

ሀ.________________________________________

ለ.______________________________________________________________

4.የነህምያ ምላሽ እርሱ ላይ የቀረቡት ክሶቹ ተቀባይነት የሌላቸው የውሸት ውንጀላዎች መሆናቸውን ማሳየት ነበር፡፡ “እናንተ በውሸት በአእምሮአችው የፈጠራችኋቸው ናቸው፡፡” የእነርሱ ፍላጎትን ምን ለማድረግ ነበር (ቁጥር 9ለ)?

____________________________________________________________________

5. ነህምያ ምን አይነት እርምጃን ወሰደ (ቁጥር 9ለ)?

____________________________________________________________________

6.ተቃውሞ የመጣው ከአይሁድ ማህበረሰብ ውጭ ከሚገኙ ሰዎች ብቻ አልነበረም፡፡ በነህምያ ህይወት እና ባህሪይ ላይ የተጋረጠው አደጋ ምን ነበር (ቁጥር 10-13)?

____________________________________________________________________

____________________________________________________________________

____________________________________________________________________

**ማሰላሰል**:

በቁጥር 2 ላይ ሰዎቹ እርሱን ለመጉዳት እያሰቡ እንደሆነ ነህምያ አውቋል፡፡ በቁጥር 12 ላይ ደግሞ እግዚአብሄር ሸማያን እንዳላከው ተገንዝቧል፡፡ ይህንን እንዴት ሊያውቅ ቻለ? ሰው ነገረው ወይንስ እነርሱ በዚያን ስፍራ ሊጎዱት እንደፈለጉ ገመተ? ምንአልባት ሰንበላጥ እና ጦቢያ ያንን ሊያደርጉ ይችላሉ ብሎ መገመት ይቻል ይሆናል፤ ነገር ግን እንዴት የእግዚአብሄርን ሰዎች እንዲያጠቁ ጠላት በገንዘብ ወገናቸውን ሊገዛ ይችላል ብሎ መገመት ይቻላል? በግልፅ የምናየው ግን ጠላት ሰርጎ በመግባት የእግዚአብሄርን ሰዎች ለማሳት እና ለማሸማቀቅ እና የነህሚያን ስም ለማጥፋት ከፍተኛ ጥረትን ሲያደርግ ነው፡፡ 1.የሚገርመው ነገር ነህምያ የበቀልን እርምጃ ሲወስድ አናይም፡፡ በእናንተ ታማኝነት እና ክብር ላይ ሰዎች እንደዚህ አይነት ጥቃትን ለመፈፀም ቢነሱ የምትወስዱት አማራጭ ምን ይሆን ነበር?

____________________________________________________________________

____________________________________________________________________

____________________________________________________________________

2. በጣም የሚገርም ማንነት ነው! እርሱን ለማሸማቀቅ የሚሞክሩትን ግለሰቦች እግዚአብሄር እንዲያስባቸው ነህምያ ይለምናል፡፡ እነርሱ ያደረጉትን ነገር እግዚአብሄር

እንዲያስብ ነህምያ ይጠይቃል። የእነርሱ ፍላጎት የእግዚአብሄር ህዝብ እየገነባ የሚገኘውን ስራ ለማፍረስ እና ______________________ ነው (ነህምያ 2:17ለ)።

3. ይህ ጊዜ ጥያቄን ለመጠየቅ ትክክለኛ ጊዜ ነው። የእግዚአብሄር ስራ በሚሰራበት ወቅት እኔ ከተቃዋሚዎች ጋር ሆኘ ስራውን ለማስተጓጎል እሰለፋለሁ ወይንስ የእግዚአብሄርን ስራ ከሚሰሩት ወገን ነኝ?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

4.እኔ የሌሎችን ጥረት ለማፍረስ የምፈለግ ሰው ነኝ ወይንስ የእግዚአብሄርን ስራ የምሰሩትን እየደገፍኩኝ አበረታታለሁ?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

5.አንድ አዲስ ነገር መሰራት ሲጀምር ወይንም ሊሰራ ሲታሰብ የእናንተ ስሜት፤ቃላት እና አጠቃላይ ሁኔታ ምን ይመስላል። እናንተ የተጀመረው ስራ በተሻለ ሁኔታ ተስፋፍቶ እንዲቀጥል በቅን ልቦና ትሳተፋላችሁ ወይንስ ነገሮች በአሉበት ሁኔታ እንዲቀጥል ብቻ ነው የምትፈልጉት? የሚሰማችሁን ስሜት ግለፁ:

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

**ፀሎት**:

ጌታ ሆይ አስበኝ። በሞገስህ አስበኝ። አንተ ብቻህን ፃድቅ ስለሆንክ አስበኝ። ኃጢአቴን አታስብ። የአንተን ፈቃድ ባለመፈፀሜ እንዲሁም ለባለንጀራዬ ማድረግ የሚገባኝን ባለማድረጌ ምክንያት የበደልኩትን ይቅር በለኝ። አንተ ለእኔ ያለ ፍቅር ዘላለማዊ ስለሆነ ኃጢአቴን አታስታውሰው። አንተ በፃዲቁ በአዳኜ እና በተቤዢኘ ልጅህ በእየሱስ ክርስቶስ ደም አስታውሰኸኛል። ከእየሱስ ክርስቶስ የተነሳ መልካሚቱ እጅህ ሁልጊዜ ከእኔ ጋር እንደሆነች አውቃለሁ። ታላቁ አምላክ ከእኔ ጋር መሆንህን ስለማውቅ ምንም ነገር አያስፈራኝም። ስለአስታወስከኝ አመሰግንሀለሁ።

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

**<u>ክፍል 3</u>**

**የቤት ስራ**: ነህምያ 6:15-16፤ 19ለ፤ እና ነህምያ 7:1-3 አንብቡት

***መልመጃ***:

1. የእግዚአብሄር ክንድ በተገለጠበት በ52 ቀናት ውስጥ ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቀው ስራ ምን ነበር! በምዕራፍ 6 ቁጥር 15-16 ላይ የተጠቀሱት በጠላት ተቃውሞ ውስጥ እግዚአብሄር ልጆቹን ሲያስታውሳቸው የሚሆነውን ነው።

ቅጥሩም ____________________በሀያ አምስተኛው ቀን ____________________ውስጥ ተጨረሰ። ____________________ይህን በሰሙ ጊዜ በዙሪያችን የነበሩ ____________________፥ በራሳቸውም አሳብ ____________________፥ ይህም ሥራ ____________________እንደ ተደረገ አወቁ።

ከተቃውሞው ጠንሳሾች አንዱ የሆነው ተቃውሞውን አጠናክሮ ቀጠለው (ቁጥር 19)። ጦቢያ አጠናክሮ የቀጠለው ነገር ምንድነው?

______________________________________________

2.የእየሩሳሌም ቅጥር ግንባታ ተጠናቀቀ፤ በሮቹም ተመልሰው በቦታቸው ተገጠሙ። የስራ ምድባ ተከናወነ። ግለሰቦችም ኃላፊነት ተሰጣቸው። ነህምያ የግንቡ አለቃ ስለሆነው ስለ ሐናንያን የሚናገረው ነገር ምንድነው (7 ፡ 2)?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

3.የሐናንያ አይነት ማንነት በህይወታችሁ አለ፤ከሰዎች ይልቅ እግዚአብሄርን የሚፈራ ማንነት አላችሁ? አጭር ጊዜ ውሰዱ እና ስለዚህ ሰው እግዚአብሄርን አመስግኑት።

እግዚአብሄር ለስራው ለጠራቸው ሰዎች ጥሪያቸውን በብቃት መወጣት እንዲችሉ እርሱ ሃይልን እና ብርታትን እንዲሰጣቸው ፀልዩላቸው፡፡

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

**አስተምሮ**:

በቁጥር 3 ላይ አንድ ያልተለመደ እንግዳ ነገር ሲሆን እናያለን፡፡ ለምንድነው ነህምያ ፀሃይ እስከምትሞቅ ድረስ የእየሩሳሌም በሮች አይከፈቱ ብሎ ያዘዘው? የምዕራፍ ስድስት የመጨረሻውን ቁጥር በአዕምሮአችሁ ያዙት፡፡ የተቃውሞው ስጋት እንደቀጠለ ነው፡፡ ነጋዴዎች እና ሌሎች ሰዎች በጊዜ ስራቸውን እንዲያከናውኑ የከተማው በር ቀደም ብሎ ቀኑ መንጋት ሲጀምር መክፈት የተለመደ አሰራር ነው፡፡ ነህምያ ግን በጣም ጠንቃቃ ነበር፡፡ እርሱ የእየሩሳሌም በሮች እንዳይከፈቱ ያደረገበት ምክንያት ተቃዋሚዎች በድንገት ወደከተማው በመግባት ሽብርን እንዳይፈጥሩ በማሰብ ነው፡፡
የሚቀጥሉት በርካታ ቁጥሮች (4-69) ከምርኮ ምድር የተመለሱትን ሰዎች የትወልድ ሃረግ ይዘረዝራል፡፡ ከዘሩባቤል እና ኢያሱ ጋር የተመለሱ ሰዎች ስም ዝርዝር (ቁጥር 7)፡፡ ስለእነርሱ በመፅሐፈ እዝራ ላይ እናገኛለን፡፡ ይህ ትውልድ ሃረግ ለእኛ ጠቃሚ መስሎን አይታየን ይሆናል፡፡ ነገር ግን ለአይሁዳውያ የእነርሱ ቤተሰቦች የእስራኤል የዘር ግንድ ያላቸው መሆኑን ለማሳየት የግድ አስፈላጊ ነው (ቁጥር 61)፡፡ ቁጥር 64 የሚያሳየን የትውልድ ሃረጋቸው ተፈልጎ የጠፉ ሰዎች ከክህነት አገልግሎት መታገዳቸውን ነው ፡፡

ከቁጥር 70-72 ባለው ክፍል ውስጥ የምንመለከተው የአባቶች አለቆችን ለጋስነትን ነው፡፡ ለስራው ብቻ ሳይሆን የሰጡት ለግምጃ ቤት ጭምርም ነው፡፡ እነርሱ የሰጡት ብር፤ወርቅ፤ የካህናት ልብሶችን እና ሌሎች ስጦታዎችንም ሰጡ፡፡ የእግዚአብሄር ቤተ መቅደስ ግምጃ ቤት የአገሪቱን ሃብት የያዘ ነው፡፡

**የቤት ስራ**: ነህምያ 8 አንብቡት

**መግቢያ**:

የቅጥሩ ግንባታ ከተጠናቀቀ በኋላ ህዝቡ ወደ ቤቶቻቸው እና ከተሞቻቸው የራሳቸውን ኑሮ መኖር እንዲጀምሩ እንዲሄዱ ተደረገ፡፡ አሁን ደግሞ ህዝቡ ተሰባስቦ ህጉ የሚነበብበት ጊዜ ደረሰ፡፡ እዝራ ከነህምያ ጋር በአንድ ወቅት የነበረ ሰው ቢሆንም እርሱ ወደ እየሩሳሌም የደረሰው ከነህምያ 13 ዓመታት ቀድሞ ነው፡፡ የእዝራ ዋና ኃላፊነት የሙሴን ህግ ለህዝቡ ማስተማር ነበር፡፡

**መልመጃ**:

1.በቁጥር 2 ላይ እዝራ ምን አደረገ?

______________________________________________

2.እርሱም ድምፁን ከፍ አድርጎ ከ ____________________ እስከ ______________________________ ድረስ አነበበ፡፡ ከዚያ ህዝቡም በሙሉ ______________________________________________

3. ስለወቅቱ አጠቃላይ ሁኔታ መግለጫን ይሰጠናል፡፡ እዝራም ወንድ እና ሴቶች በነበሩበት ስፍራ ከፍ ብሎ ቆመ፡፡ እዝራ የቆመው የት ነው (ቁጥር 4)? __________________________ ወንዶች እና ሴቶች በቦታው ነበሩ፡፡ እዝራ የቆመው የት ነው (ቁጥር 4)?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

4. በቁጥር 5 ላይ እዝራ ምን አደረገ?

______________________________________________

ህዝቡስ ምን አደረጉ?

______________________________________________

5.በቁጥር 6 ላይ እዝራ ምን አደረገ ?

______________________________________________

ህዝቡስ ምን አደረጉ?

______________________________________________

6.የሌዋውያን ስራ ምን ነበር (ቁጥር 7-8)?________________________________

_____________________________________________________________

_____________________________________________________________

7.ህዝቡም ህጉን በሰሙ ጊዜ ምን ያህል ከእግዚአብሄር ህግ ተልይተው እና ጠፍተው እንደነበር ስያስተውሉ አለቀሱ። እዝራ፤ነህምያ እና ሌዋውያን ግን የፈለጉት ቀኑ የምስጋና እና የደስታ እንዲሆን ነው (ቁጥር 9)። ህዝቡ እንዲያደርጉ የተነገራቸው ነገር ምን ነበር (ቁጥር 10-11)?

_____________________________________________________________

_____________________________________________________________

_____________________________________________________________

8.ለህዝቡ ታላቅ የምስጋና እና የደስታ በዓልን እንዲያደርጉ ያደረጋቸው ነገር ምን ነበር (ቁጥር 12)?

_____________________________________________________________

_____________________________________________________________

_____________________________________________________________

**አስተምሮ**:

አንድ ቀን የአባቶች ቤት አለቆች፤ካህናት እና ሌዋውያን በእዝራ ዙሪያ ተሰባሰቡ (ቁጥር 13-18)። እነርሱም ከህጉ ንባብ የተረዱት ነገር እያንዳንዱ ቤተሰብ በቤታቸው ፤በአደባባይ ላይ፤ በቤተ መቅደሱ ጊቢም ውስጥ ዳስን መስራት እንዳለባቸው ተገነዘቡ። ዳሱ ደግሞ የተሰራው ከዛፍ ቅርንጫፎች ነው። ከምርኮ የተመለሰው ህዝብ ዳስ ሰርተው ለበርካታ ቀናት ይኖሩባቸው ነበር። እነዚህ ዳሶች እስራኤላውያ ከግብፅ ባርነት እግዚአብሄር ነፃ በአወጣቸው ጊዜ በዳስ ወስጥ እንደኖሩ የሚያስታወሳቸው ነው (ዘሌዋውያ 23:33-43)። ዳሶቹ ህዝቡ ከእግዚአብሄር ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንደገና ማደሳቸውን የሚያመለክት ውጫዊ ምልክት ነው። ይህ ሳምንት የዳስ በዓል ተብሎ ይታወቃል። በእዚህን ወቅት እዝራ በየእለቱ ከእግዚአብሄር ህግ መፅሐፍ ሲነብ ህዝቡም በታላቅ ደስታ ይሰሙት ነበር። በስምንተኛው ቀን ደግሞ ጉባኤ ተካሄደ።

**<u>ክፍል 4</u>**

***መግቢያ***:

***ይህንን ጥናት በበለጠ ለመረዳት የነህምያ መፅሐፍን ጥናት እንደገና ከልሱት። የዚህን ጊዜ በደንብ ይህንን እንድትረዱ ይረዳችኋል።***

***መልመጃ***:

1.እነዚያ የእስራኤል ትውልዱ የሆኑት ሰዎች የእግዚአብሄርን ህግ ለመስማት ተሰባስበዋል፤የእነርሱን እና የአባቶቻቸውን ኃጢአት እና ክፋትን ሁሉ እየተናዘዙ ንስሃ ሲገቡ ነበር። በቁጥር 1 መሰረት የለበሱት ምን ነበር? ____________________

________________________________________________________________

2.ህዝቡም በመቆም ከዘላለም እስከ ዘላለም የሚኖረውን እግዚአብሄር አምላክን ያመሰግኑ ነበር። እንደሚከተሉት ቁጥሮች መሰረት ህዝቡ ያስታወሱት ነገር ምንድነው:

ሀ.ቁጥር 5ለ-6:

________________________________________________________________

________________________________________________________________

ለ.ቁጥር 7-8:

________________________________________________________________

________________________________________________________________

ሐ.ቁጥር 9-12:

________________________________________________________________

________________________________________________________________

መ.ቁጥር 13-15:

________________________________________________________________

________________________________________________________________

3.በሚከተሉት ቁጥሮች ውስጥ እነርሱም ስለአባቶቻቸው እና ቅድመ አያቶቻቸው አካሄድ እንዲያውቁት ተደርጓል (ቁጥር 16-17ሀ):

________________________________________________________________

________________________________________________________________

4.በቁጥር 17ለ እና 18 ደግሞ እግዚአብሄር ማን እንደሆነ እንዲያውቁ ተደረገ:

ሀ._________________________________________________________________

ለ._________________________________________________________________

ሐ._________________________________________________________________

መ._________________________________________________________________

ሠ._________________________________________________________________

5.ህዝቡ ማስታወስ የሚገባቸውን ነገር በተከታታይ እንዲያስታውሱ የተደረገው ምንን ነው:

ሀ.ቁጥር 18:

_________________________________________________________________

ለ.ቁጥር 19-21:

_________________________________________________________________

_________________________________________________________________

ሐ.ቁጥር 22-25:

_________________________________________________________________

_________________________________________________________________

_________________________________________________________________

6.እንደገና በቁጥር 26-27ሀ ውስጥ እነርሱ የቅድመ አያቶቻቸውን መንገድ እንዲያስታውሱ ተደርጓል: ______________________________________________

_________________________________________________________________

_________________________________________________________________

_________________________________________________________________

እግዚአብሄር በእርሱ ታላቅ ርህራሄ እነርሱን ነፃ የሚያወጡ ነፃ አውጪዎችን በመስጠት ከብዙ መከራ ታደጋቸው (ቁጥር 27ለ)።

7.ይህ የታሪክ እሽክርክሪት እንደገና ተከሰተ (ቁጥር 28):

ሀ.ህዝቡ ምን አደረጉ?

________________________________________________________

ለ.እግዚአብሄርስ ምን አደረገ?

____________________________________________________________

8.በቁጥር 29-30 ውስጥ እግዚአብሄር አስጠነቀቀ፤ እነርሱ ግን

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

9.በቁጥር 31 ላይ እግዚአብሄር ግን

________________________________________

________________________________________

10.ምንም እንኳን ህዝቡ ያደረጉት ነገር ሁሉ እግዚአብሄርን የሚያስቆጣ ቢሆንም እርሱ ግን ፃዲቅ ሲሆን የሚያደርገውን ነገር ሁሉ በታማኝነት ሲያደርግ ነበር (ቁጥር 33)፡፡ ከዚህ በፊት አባቶቻቸው እና ቅድመ አያቶቻቸው በፈፀሙት ኃጢአት ምክንያት ለምርኮ ቢዳረጉም የእግዚአብሄር ህዝብ አሁን ያሉበት ሁኔታ ምን ይመስላል (ቁጥር 36-37)?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

**ማሰላሰል**

እንዴት ያለ አስቸጋሪ መገለጥ ነው፡፡ እንዴት ያለ አሳዛኝ ሁኔታ ነው፡፡ እግዚአብሄር ለአብረሃም የገባውን የተስፋ ቃል በማሰብ ለህዝቡ መልካም የሆነውን ሁሉ ያደርግ ነበር፡፡ አሁን ቅሬታ ብቻ ነው የቀረው፡፡ አሁን ቀድሞ የእነርሱ በነበረችው ምድር ባሪያዎች ሆነዋል፡፡ ሃብትም እና ንብረትም የላቸውም፡፡ አሁን ማድረግ የሚገባቸው ነገር ምንድነው? በኦሪት ዘፍጥረት እግዚአብሄር ለአብረሃም ዘርህ እንደ ሰማይ ከዋክብት የበዛ ይሆናል በማለት የገባለት የተስፋ ቃል ምን ሆነ? እነርሱ አሁን ቅሬታ ብቻ ናቸው፡፡ የእነርሱ እንዲሆን እግዚአብሄር የሰጣቸው ምድር አሁን የፋርስ መንግስት ግዛት ሆኗል፡፡ አሁን እነርሱ በታላቅ መከራ ውስጥ ሆነው ኑሮአቸውን በባርነት ይመራሉ፡፡ የታላቅ ንብረት ባለቤት የነበረው ህዝብ አሁን የሚያገኙትን ሁሉ ለፋርስ ንጉስ በግብር መልክ ያቀርባሉ፡፡ ባለስልጣኖቻቸው እና መኳንንቶቻቸው ሁሉ ለንጉሱ ባለመታዘዝ ተከስሰዋል፡፡ ይህ ደግሞ እግዚአብሄር ከገባው የተስፋ ቃል ጋር ሊሄድ የማይችል ጉዳይ ነው፡፡

ንስሃ ህይወትን እንደገና ለመጀመር ትክክለኛ ስፍራ ነው። ኃጢአት ሁልጊዜ በሰው እና በእግዚአብሄር መካከል የሚገባ እና ግንኙነትን የሚያበላሽ ነው። ይህ እንቅፋት ደግሞ የሚወገደው በንስሃ፤በቅዱሱ እግዚአብሄር ላይ የተፈፀም በደል በመናዘዝ እና እርሱ እንዴት መኖር እንደሚገባን እንደሚፈልገው አይነት ኑሮ ስንኖር ነው። ኑዛዜ ማለት በእግዚአብሄር ፊት ኃጢአተኛነታችንን በእግዚአብሄር ፊት ማስታወቅ ነው። ለምሳሌ በመፅሐፈ ነህምያ 9:16 እና 17 ላይ እስራኤላውያን አባቶቻቸው እና ቅድመ አያቶቻቸው ግትር፤ልበ ደንዳና እና ለእግዚአብሄር ህግ የማይታዘዙ እንደነበሩ በመጥቀስ እየተናዘዙ ንስሃ ይገቡ ነበር። እነርሱ ግን ጌታን ለማዳመጥ እና ትዕዛዛቱን ለማስታወስ ፈቃደኛ አልሆኑም። ቁጥር 26 ደግሞ ሌላ ምሳሌ ነው። እነርሱ የማይታዘዙ እና በእግዚአብሄር ላይ አመፀኞች ናቸው። እነርሱ የእግዚአብሄርን ህግ ቸል በማለት አስከፊ በሆነ መልኩ እርሱን የመሳደብ ተግባርን ፈፀሙ።

በዚህ ሁሉ መካከል እግዚአብሄር አልተለወጠም። ምንም እንኳን ህዝቡ ከፈቃዱ ውጭ ቢመላለሱም እግዚአብሄር ግን ይቅር አላቸው። እርሱ ለእነርሱ ርህሩህ እና ቸር፤ ለቁጣ የዘገየ እንዲሁም ፍቅሩ ማብቂያ የሌለው ነው። እርሱ አልጣላቸውም፤ ነገር ግን ከጠላቶቻቸው እጅ በተደጋጋሚ ነፃ በማውጣት አዳናቸው። እግዚአብሄር ቸር፤ ይቅር ባይ፤ ፃዲቅ እና ታማኝ አምላክ ነው። ወደዚህ አምላክ ኃጢአታችንን ልንናዘዝ እና ይቅርታን ከእርሱ ለመቀበል መበርታት አለብን። ወደዚህ አምላክ የምንቀርብበት ምክንያት ኃጢአታችንን ደግሞ ስለማያስብ ነው (ትንቢተ ኤርሚያስ 31:34)። ኃጢአታችንን ከእኛ ላይ ስለሚያስወግደው የእኛን ጥፋት ደግሞ አያስበውም። እርሱ ልጁን እየሱስ ክርስቶስን በእኛ ምትክ በመላክ በደላችንን እና ኃጢአታችንን በመሸከም የእግዚአብሄርን ቁጣ ከእኛ ላይ አራቀ። እግዚአብሄር አብ ልጁን እየሱስ ክርስቶስን የሰጠን በእኛ እንዲፈርድ ሳይሆን እኛን እንዲያድነን ነው! የዮሐንስ ወንጌል 3:17-18ሀ ይህንን የምስራች ይናገረናል: “ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ፥ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና። በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፤” አስደናቂ ለሆነው ስጦታው ስለ ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሄርን እናመስግን።

ክፍል 4

***መግቢያ***

የእስራኤል ህዝብ የእነርሱን፣ የአባቶቻቸውን እና የቅድመ አያቶቻቸውን ኃጢአት ተናዘዙ፡፡ እግዚአብሄር ህጉን በመጠቀም የእነርሱን ኃጢአትን እና የተሳሳተ ስራ አሳያቸው፡፡ ህጉ በእግዚአብሄር መንፈስ እርዳታ እንደ መስተዋት በመሆን አይኖቻቸውን በመክፈት ምን ያህል ከእርሱ ፈቃድ እና አላማ እንደተለዩ እና እንደጠፉ አሳያቸው፡፡ ህጉን በመጠቀም እግዚአብሄር በቸርነቱ እና በምህረቱ ወደ እርሱ በንስሃ እንዲመለሱ አደረገ፡፡ እነርሱም ለመታዘዝ ፈቃደኛ ሆኑ፡፡ እነርሱ እግዚአብሄር ከህይወታቸው የሚፈልገውን በታማኝነት ለማድረግ ቃል ገቡ፡፡

**የቤት ስራ**: ነህምያ 10:28-39 አንብቡት

***መልመጃ***: በሚቀጥሉት ቁጥሮች ውስጥ ህዝቡ የገባውን ቃል ኪዳን ዋና ሃሳብ ለዩ:

1.ቁጥር 30:

______________________________________________

2.ቁጥር 31:

______________________________________________

3.ቁጥር 32-33:

______________________________________________

______________________________________________

4.ቁጥር 34:

______________________________________________

5.ቁጥር 35:

______________________________________________

6.ቁጥር 36:

______________________________________________

7.ቁጥር 37-39:

______________________________________________

**ትግበራ**:

1.ጥቂት ጊዜን ወስዳችሁ በምዕራፍ 10 መጨረሻ ላይ ያለውን ዓረፍተ ነገር ተመልከቱ: "

ከቶ አንተውም።"

2.የአይሁድ ማህበረሰብ ለእግዚአብሄር ቤት እና በዚያ ለሚያገለግሉት ሰዎች የሚያስፈልገውን ሁሉ ለማድረግ የተሰጡ ሆኑ። የእግዚአብሄር ቤት ሁኔታ ለአይሁድ ማህረሰብ መንፈሳዊ ህይወት የሚኖረው አስተዋፅኦ ምንድነው?

3.እንደ እግዚአብሄር ቃል ተማሪነታችን ማወቅ የሚባን በርካታ ነገሮች አሉ። ስለ አምልኮ ህይወት፤ስለ እግዚአብሄር ቤት ፤ ከባለእንጀራችሁ ጋር ስለሚኖራችሁ ግንኙነት፤ስለአገልግሎት አሁን ያጠናችኋቸው ጥናቶች ምን አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል?

4. በ2 ቆሮንቶስ 6:16-18 ውስጥ ስለ እግዚአብሄር ቤተ መቅደስ ይናገራል። እነዚህን ጥቅሶች አንብቡ እና እግዚአብሄር ምን አይነት ህብረት ከእናንተ ጋር ማድረግ እንደሚፈልግ ተመልከቱ። እርሱ የሚናገረው "በእነርሱ እኖራለሁ በመካከላቸውም እመላለሳለሁ፥ አምላካቸውም እሆናለሁ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ።" በማለት ከተናገረ በኋላ "እኔም እቀበላችኋለሁ፥ ለእናንተም አባት እሆናለሁ እናንተም ለእኔ ወንድ ልጆችና ሴት ልጆች ትሆናላችሁ" ይላል።

ይህ አባባል ለእናንተ ምን ማለት ነው?

5.ህዝቡ ለነህምያ “የጌታ አምላካችንን ቤት ችላ አንለውም” ብለው የተናገሩትን በአዕምሮአችሁ ያዙትና ይህ አባባል ለእናንተ እርሱ እናንተን የራሱ ቤተ መቅደሱ ከማድረጉ አንፃር እንዴት ይህንን እርሱ ሊኖርበት የመረጠውንን ሰውነታችሁን ወይንም የእግዚአብሄር ቤተ መቅደስ ችላ እንደ ማትሉት ወይንም ችላ ማለት እንደምትችሉ አብራሩ?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

6.እንደ ቤተ ክርስትያን አባልነታችሁ ይህ አባባል እንዴት የእግዚአብሄር ህዝብ አንዱ ለአንዱ እንክብካቤ ማድረግ እንዳለበት ይናገራል?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

**ፀሎት**:

እግዚአብሄር በመንፈሱ በኩል ህጉን በመጠቀም ልባችንን ለኑዛዜ እና ንስሃ ስለሚያዘጋጅ አመስግኑት፡፡ የእግዚአብሄር ቤት ስለሆነው ህዝቡ ወይንም ቤተክርስትያን እና ስለ ሰውነታችሁም አመስግኑት፡፡ እግዚአብሄርን በቤቱ ቅናት እና በአገልግሎት ፍቅር ልባችሁን እንዲያቀጣጥለው ጠይቁት፡፡ እናንተን ቤተ መቅደሱ እና አገልጋዩ አድርጓችሁ ስለመረጠ እንዴት አድርጋችሁ እርሱ የሚፈልገውን አይነት ህይወት መኖር እንደምትችሉ እና እንዴት አድርጋችሁ እርሱ የሚፈልገው አይነት አገልግሎት ማገልገል እንደምትችሉ ጠይቁት፡፡

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

**<u>ክፍል 5</u>**

***መግቢያ***:

በምዕራፍ 11 ላይ የህዝቡ መሪዎች በእየሩሳሌም ውስጥ እንዴት መኖር እንደጀመሩ እንመለከታለን፡፡ ሌሎች ሰዎች ግን እጣ ተጣጣሉ፡፡ ቅድስት ከተማን እየሩሳሌምን እና ነዋሪዎችዋን ለመጠበቅ እንዲያመች ከአስር ቤተሰብ አንዱ በእየሩሳሌም እንዲኖሩ ተወሰነ፡፡ የተቀሩት ሰዎች ግን በይሁዳ በሚገኘው በቅድመ አያቶቻቸው ርስት ላይ ሰፈሩ (ቁጥር 20) ፡፡

ነህምያ 12:1-26 የሚናገረው ከዘሩባቤል እና ኢያሱ ጋር ከምርኮ ስለተመለሱት ካህናት እና ሌዋውያን የትውልድ ሀረግ ነው፡፡ እዚህ ጋር ማስተዋል ያለባችሁ እነዚህ ሰዎች ካህናቱ እና ሌዋውያኑ የእርሱን ህዝብ በዚህ አገልግሎት ለማገልገል እግዚአብሄር ለዚህ አገልግሎት ከመረጠው ከሌዊ ጋር በትውልድ መገናኘት አለባቸው፡፡

**የቤት ስራ**: ነህምያ 12:27-47 አንብቡት

***መልመጃ***:

1.የእየሩሳሌም ቅጥሩ ምረቃ ጊዜ ደረሰ!  ይህንን ታላቅ በዓል እንዲመራው የተጠራው ማነው (ቁጥር 27)?

______________________________________________

በዚህ በዓል ላይ የተሰበሰቡት ሌሎቹ እነማን ናቸው (ቁጥር 28)?__________________

______________________________________________

2.በበዓሉ ውስጥ የተካተተው ነገር ምንድነው (ቁጥር 27)?________________________

______________________________________________

3.ካህናቱ እና ሌዋውያኑ ያደረጉት የመጀመሪያው ነገር ምንድነው (ቁጥር 30)?

______________________________________________

______________________________________________

4.በቁጥር 31-39 ላይ ነህምያ በዋናነት ያዘጋጀው ነገር ምንድነው፡፡ ሁለት የመዘምራን ቡድኖችን እና ከይሁዳ የሆኑት መሪዎችን በመያዝ ወደ ቅጥሩ ሄደ፡፡ ግማሾቹ ወደ ደቡብ

ሲሄዱ ቀሪዎቹ ግማሾቹ ደግሞ ወደ ሰሜን ሄዱ። ወደ ደቡብ የሄደው የመዘምራን ቡድን ________________________የዜማውን ዕቃ ይዘው ሄዱ ________________________በፊታቸው ነበረ። (ቁጥር 36).

5.ወደ ሰሜን የሄደውን የመዘምራን ቡድን የተከተለው ማነው (ቁጥር 38)?

________________________________________________________________

6.በቁጥር 40 ላይ ደግሞ ነህምያ እና ሁለቱ የመዘምራን ቡድን ስፍራቸውን ________________________________ያዙ

7. እንደ ቁጥር 43 መሰረት የቀኑ ሁኔታ ምን ይመስል ነበር?____________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

8.ቁጥር 44-47 እንደገና የሚያስታውሱን ነገር እግዚአብሄርን ለሚያገለግሉት ሰዎች ህዝቡ ስለሰጠው ስጦታ ነው። ለእቃ ቤቶቹም ____________________ (ቁጥር 44)።

9.ለማን ነው ስጦታዎቹ የተለዩት (ቁጥር 47)? ______________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

**ማሰላሰል**:

የህንፃ ወይንም የማህበረሰብ ፕሮጀክት ወይንም ሌላ ህንፃ ወይንም መንገድ ወይንም ድልድይ ሲመረቅ በምረቃው በዓል ላይ ተገኝታችሁ ታውቃላችሁ? ሰዎች በደስታ በዓሉን ለምን እንደሚያከብሩ አስተውላችኋል? አንዳንድ ሰዎች ለመደሰት ዝግጁ ናቸው። ይሁን እንጂ የሆነውን ነገር ሁሉ ለማስታወስ ትችላላችሁ፤ ህዝቡም በጥረቱ ያከናወነው ነገር በመጠናቀቁ እና የተሰራው ነገር የሚሰጣቸውን ጥቅም እና ዝና እያሰቡ ምረቃውን በደስታ ያከብሩታል። ያለጥርጥር በምረቃው በዓል ላይ የሚገኙት ሰዎች ስራው እንዲሰራ ሃሳብ ያቀረቡ፤ሌሎች ደግሞ የሚሰራውን ስራ ፕላን የሰሩ፤ ሌሎች ደግሞ በግንባታ ስራው ላይ የተሳተፉ እና ሌሎች ደግሞ የምረቃውን በዓል እያስተባበሩ የሚገኙ ሊሆኑ ይችላሉ።

ይህ ሁኔታ በተማሳሳይ መልኩ የቤተ ክርስትያን ህንፃ ወይንም የእግዚአብሄር ስራ ሲሰራ የሚሆን ተግባር ነው። በግንባታው ስራ ላይ የተሰማሩ የተለያዩ ባለሙያዎች እና የተጋበዙ ባለስልጣናት እና እንግዶች በምረቃው በዓል ላይ ይገኛሉ። የምረቃ ስነስርዓቱም

የሚመራው በቄሶች፤ መዘምራን እና በማህበረ ምዕመናኑ መሪዎች ነው፡፡ ሙዚቀኞችም የተለያየ ዘመናዊ እና ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን በመያዝ ህዝቡ በዝማሬ እግዚአብሄርን በደስታ እንዲያመሰግኑ እና እንዲያከብሩ ይመሩታል፡፡ ይህ የምረቃ የአከባበር በዓል ለቀናትም ጭምር ሊቆይ ይችላል፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ የእናንተ ልምምድ ምን ሊሆን ይችላል? ከእግዚአብሄር ህዝብ ጋር ለእንደዚህ አይነቱ የምስጋና በዓል ስትሰባሰቡ የሚሰማችሁ ነገር ምንድነው? ሁኔታውስ ምን ይመስላል?_______________________________________________________

____________________________________________________________________

____________________________________________________________________

____________________________________________________________________

የእየሩሳሌም ደስታ ከርቀት ይሰማ ነበር፡፡

**አስተምሮ**:

በምዕራፍ 13 ላይ መቼ ወይንም ለምን እንደሄደ ባናውቅም ነህምያ የእየሩሳሌም ቅጥር ከተመረቀ ከተወሰነ ጊዜ በኂላ ወደ ንጉስ አርጤክስስ እንደተመለሰ ተፅፏል (ቁጥር 6) ፡፡ እርሱ በእየሩሳሌም ለ12 ዓመታት ኑሯል፡፡ ነህምያ ወደ ንጉሱ የተመለሰበት ምክንያት ቀድሞ ወደ እየሩሳሌም ከመምጣቱ በፊት በነበራቸው ስምምነት መሰረት ለሆን ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ ክፍሉ የሚናገረን ነገር ከተወሰነ ጊዜ በኂላ ወደ እየሩሳሌም መመለሱን ነው፡፡

ምዕራፍ 13 ሰዎች ለማንበብ ብዙ ጊዜ አይበረታቱም፡፡ በዚህ ዘመን ሰዎች መስማት የሚፈልጉት ነገር “ሰዎቹ ዘመናቸውን ሁሉ ደስተኛ ሆነው ኖሩ” የሚለውን ዓይነት ወሬን ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ወላጆቻቸው በፈፀሙት ጥፋት ሁሉንም አጥተው በምርኮ ምድር ኖረው የተመለሱትን ስናስብ የተለየ ነገር ልናስብ እንችላለን፡፡ ይህ ክፍል የሚናገረው ነገር ነህምያ ከንጉሱ ዘንድ መመለሱን ነው፡፡

**የቤት ስራ**:

ነህምያ 13 አንብቡት፡፡ ምዕራፉን ስታነቡት ጣታችሁን በነህምያ 10:28-39 አድርጋችሁ አንብቡት፡፡

***መልመጃ***:

1.በሙሴ ህግ ውስጥ እንደሚገኝ የታወቀው ነገር ምንድነው (ቁጥር 1)?

________________________________________________

________________________________________________

***ማስታወሻ*** የግርጌ ማጣቀሻን የምትመለከቱ ከሆነ ህጉ በኦሪት ዘዳግም 23:3-5 ውስጥ እንደሚገኝ ማወቅ ትችላላችሁ፡፡ ስለሁኔታው ደግሞ በኦሪት ዘሁልቁ 22:3-11; 23:7 ውስጥ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡

2.ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ ምንድነው (ቁጥር 2)?

________________________________________________

________________________________________________

3.ስለዚህ ህግ ህዝቡ የሰጠው ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 3)?

________________________________________________

4.በቁጥር 4-5 ላይ የተከናወነው ነገር ነህምያ እየሩሳሌም በአልነበረበት ወቅት ነው፡፡ ዋናው ሰው ወይን ገፀ - ባህሪይ ማን ነው? ____________________ እርሱ ካህን ሲሆን ሃላፊነቱ ደግሞ ____________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

5.ኤልያሴብ ከማን ጋር ነው የተወዳጀው (ቁጥር 4)?

________________________________________________

6.ስለ እርሱ ምን የምታስታውሱት ነገር አለ?

________________________________________________

________________________________________________

ለመከለስ እንዲያመቻችሁ ነህምያ 4:3, 7; 6:17-19 ተመልከቱ፡፡

7.ለእርሱ ኤልያሴብ በእግዚአብሄር ቤት ውስጥ ምን አደረገለት (ቁጥር 5)?

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

8.ነህምያ ወደ እየሩሳሌም ተመልሷል፡፡ ስለሁኔታ የእርሱ ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር7-9)?

________________________________________________

9.ለምንድነው ነህምያ ኤልያሴብ ለጦብያ የማረፊያ ስፍራ ስለሰጠው ነህምያ በእጅጉ ያዘነው (ነህምያ 4:3)?

10.ከዚህ ቀጥሎ ነህምያ የተረዳው ነገር ምንድነው (ቁጥር 10)?

ሀ.ነህምያ የገሰፀው ምንን ነው (ቁጥር 11)?

ለ.ሁኔታውን እንዴት ነው ያቃለለው (ቁጥር 12-13)?

11.ከዚህ ቀጥሎ ነህምያ የተረዳው ነገር ምንድነው (ቁጥር15-16)?

ሀ.ነህምያ የገሰፀው ነገር ምን ነበር (ቁጥር 17-18)?

ለ.ሁኔታው የተቃለለው እንዴት ነበር (ቁጥር19-22ሀ)?

12.ነህምያ የሆነ ነገር እንዳለ አውቋል ፡፡ በዚህን ሰዓት የሆነው ነገር ምንድነው (ቁጥር 23-24)?

ሀ.ነህምያ የገሰፀው ነገር ምድነው (ቁጥር 25-27)? ______________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

ለ.ሁኔታው የተቃለለው እንዴት ነበር (ቁጥር 28, 30)? ___________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

13.ነህምያ እግዚአብሄር ፀጋውን እና ምህረቱን እንዲያደርግ በምዕራፉ ውስጥ በተከታታይ ይፀልይ ነበር:

ሀ.ቁጥር 14: "አምላኬ ሆይ _________________________________________________ ::"

ለ.ቁጥር 22ለ: "…አምላኬ ሆይ _______________________________________________ ::"

ሐ.ቁጥር 31ለ: "…አምላኬ ሆይ __________________________________________::"

14. በቁጥር 29 ነህምያ ስለእግዚአብሄር ፍትህ ይለምን ነበር: " ______________ ________________________________________________________________አስባቸው::"

**ማጠቃለያ**:

ህጉ ተነበበ (ነህምያ 8):: ህዝቡ ኃጢአታቸውን ተናዘዙ (ነህምያ 9):: የሚገዙበትን ቃል ኪዳን እርስ በእርሳቸው አደረጉ (ነህምያ 10):: ቅጥሩ ተመረቀ (ነህምያ 12):: ነህምያ ለተወሰነ ጊዜ ከእየሩሳሌም ወደ ንጉስ አርጤክስስ ሄደ ሲመለስ ምን ነገር ገጠመው (ነህምያ 13)? ከምዕራፍ 10 እንደገና እነዚህን ቃላትን አስታውሷቸው፤ " የጌታ እግዚአብሄር አምላካችንን ቤት ቸል አንልም::" የነህምያን ተሃድሶን የማምጣት ትልቅ ፍላጎት በመመልከት እንጀምራለን:: የእግዚአብሄርን ቤት በዋናነት የመጠበቅ ሃላፊነት የነበራቸው ካህናቱ እና ሌዋውያኑ ልክ እንደ ቅድመ አያቶቻቸው እነርሱም በፍጥነት ኃጢአትን ፈፀሙ::

ታሪክ ራሱን የሚደግምበት ሁኔታ አለ:: የቅድመ አያቶቻቸው ኃጢአት ተጠልቶ ብዙም ሳይቆይ ተከታዩ ትውልድ ተመሳሳይ ኃጢአትን ሲሰራ እንመለከታለን:: የእግዚአብሄር

ህዝብ ከስህተቱ የሚማረው መቼ ነው? ራሳችንን “መቼ ነው ከስህተታችን የምንማረው?” ብለን እስከምንጠይቅ ድረስ ይህንን ጥያቄ ሌሎችን መጠየቅ ቀላል ነው፡፡ ኃጢአት ወደ አለም ሁሉ ገብቷል፡፡ ማንኛውም ፍጥረት የሰው ልጆችን ጨምሮ በኃጢአት ተበክሏል፤ክፋት እና ውድመት በአለም ውስጥ ተበራከተ፡፡ ይሁን እንጂ እግዚአብሄር ልክ ርህሩህ አባት ህፃን ልጁ መኪና ወደሚበዛበት መንገድ ሲሮጥ እንዲመለስ በፍቅር እንደሚጣራ ሁሉ እግዚአብሄርም ህዝቡ ወደ እርሱ እንዲመለሱ ይጠራል፡፡

የእርሱ ለሆኑት የእግዚአብሄር የፍቅር ጥሪ እንዴት ታላቅ ነው! ምንም እንኳን የእስራኤላውያ አባቶች እና ቅድመ አያቶች አመፀኞች እና የማይታዘዙ ቢሆኑም እግዚአብሄር ግን በርህራሄ እና በምህረት ተገለጠ፡፡ ይህ የአመፀኝነት እና አለመታዘዝ እሽክርክሪት እንደገና ቀጠለ፡፡

የእነርሱ አንገተ - ደንዳና ባህሪይ የእግዚአብሄርን ህግ ላለመስማት መወሰናቸው ያጠፋው ራሳቸውን ነው፡፡ ይሁን እና እግዚአብሄር ከ70 አመታት በኂላ ለአብረሃም የገባውን የተስፋ ቃል አስታውሶ ከምርኮ ምድር ነፃ አወጣቸው፡፡

እግዚአብሄር ፃዲቅ ነው፡፡ እርሱ የተስፋ ቃሉን የሚያስታውስ እና በታሪክ መካከል ለህዝቡ ምንጊዜም መልካምን በማድረግ የሚተጋ አምላክ ነው፡፡ እኛ የተቤዠነው በእየሱስ ክርስቶስ ፅድቅ ነው፡፡ በእርሱ ፅድቅ እና ቅድስና እኛ ከሞት እና ከዲያብሎስ እጅ አምልጠን በህይወት አለን፡፡ እኛን ውድ እና ቅዱስ በሆነው በገዛ ደሙ ገዝቶናል፡፡ ይህንን ያደረገው ደግሞ ከእርሱ ጋር በእግዚአብሄር መንግስት ውስጥ ለዘላለም እንድንኖር ነው፡፡ የእርሱ የማዳን ስራ ዛሬም ቀጥሏል፡፡ ሰዎች ሁሉ ወደ እርሱ እንዲመለሱ ጥሪውን ያቀርባል፡፡ የእርሱ ቅዱስ ፍላጎት ሰዎች ሁሉ እንዲድኑ እና እውነትን እንዲያውቁ ነው፡፡ አሁንም እንደገና በትህትና የምንለው ነገር “የእግዚአብሄር ፍቅር እንዴት ታላቅ ነው!”

## የትምህርቱ ክለሳ

# የእግዚአብሄር ፅድቅ የእኛ መቤዠት

## ክለሳ

የምስራች!  የእግዚአብሔር ፅድቅ የእኛ መቤዤት የሚለውን ጥናት አጠናቅቃችኋል፡፡ ከበርካታ የመፅሐፍ ቅዱስ ታሪኮች እና በታሪኮቹ ውስጥ ከተጠቀሱት ዋና ዋና ሰዎች ጋር ተዋውቃችኋል፡፡ አሁን ጊዜው የክለሳ ነው፡፡ ማስታወስ የሚገባችሁ ነገር ይህ ፈተና አይደለም ነገር ግን ያደረጋችሁን ጥናት እንደገና የምታስታውሱበትን እና ህይወታችሁን አቅጣጫ የምታስይዙበትን እድል የሚሰጥ ነው፡፡ መፅሐፍ ቅዱስን በአጠናችሁ ቁጥር ስለእግዚአብሄር እና ስለሰው ትክክለኛ ነገሮችን፣ መረጃን እና እውነትን ትማራላችሁ፡፡ በዚህ በ21ኛው ክፍለ ዘመን እንዴት እነዚህን እውነቶች በህይወታችሁ ላይ ተግባራዊ እንደምታደርጉ ተረድታችኋል፡፡

| ቅድመ ምርኮ | ምርኮ | ድህረ ምርኮ |
|---|---|---|
| ታሪክ | ታሪክ | ታሪክ |
| ዋና ገፀ-ባህሪይ (ያት) | ዋና ገፀ-ባህሪይ (ያት) | ዋና ገፀ-ባህሪይ (ያት) |
| እውነት/አስተውሎ | እውነት/አስተውሎ | እውነት/አስተውሎ |
| | ታሪክ | ታሪክ |
| | ዋና ገፀ-ባህሪይ (ያት) | ዋና ገፀ-ባህሪይ (ያት) |
| | እውነት/አስተውሎ | እውነት/አስተውሎ |
| | | ታሪክ |
| | | ዋና ገፀ-ባህሪይ (ያት) |
| | | እውነት/አስተውሎ |

| | | |
|---|---|---|
| | | |

**ፀሎት**

ጌታ ሆይ አንተ ፅድቅህን አሳይተሃል፡፡ ይህንን ያደረከው ለህዝብህ ለእስራኤል ትክክለኛ ተግባር ስለሆነ ነው፡፡ ምንም እንኳን እነርሱ ቢበድሉህም አንተ እነርሱን ይቅር ብለህ በርህራሄ ተገልጠህ የእነርሱ የነበረ ነገር ግን እነርሱን በማይወዱ ሰዎች ተይዞ ወደ ነበረው ወደ አገራቸው እንዲመለሱ አድርገሃል፡፡ ጌታ ሆይ አንተ በፅድቅህ ለህዝብህ መሪዎችን ፧ብርታትን እና ፅናትን በመስጠት የፈረሰውን ቤተመቅደስ እና የእየሩሳሌም ቅጥርን እንዲሰሩ አስችለሃል፡፡ እነርሱ ከባርነት ምድር ወደ አገራቸው በውርደት ሲመለሱ አንተ ግን የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ አሟላህላቸው፡፡ አንተ እነርሱን አርነት እንዳወጣህ እኔንም ከአሰረኝ ነገር ሁሉ ነፃ አውጥተኸኛል፡፡ በፅድቅህ እኔን ተቤዠተሃል፡፡ እኔን ነፃ አውጥተህ በአለም ውስጥ ነፃ እና ይቅር የተባለ ሰው ሆኜ እንድኖር አድርገሃል፡፡ እኔ ለአንተ ክብርና ምስጋናን አቀርባለሁኝ፡፡

ተጨማሪ ትምህርቶችን ከፈለጋችሁ በነፃ ከሚከተለው

የድህረ - ገፃችን ማግኘት ትችላላችሁ

የእግዚአብሄር ሰላም ከሁላችሁ ጋር ይሁን!